# የማኅበራዊ ፋይዳ ትንተና በመጽሐፈ ድጓ

ዐቢይ ሙሉቀን*

Abstract

This study titled “Analysis of Social Significance in Tsome Digua” had the objective to analyze the content of Dïggʷwa thereby attempting to show the role of the significance of the book from literary perspective. The study posed and attempted to answer the following research questions: What is the literary aspect of the book? What social issues are found in the book S'omä Dïggʷwa? What do these issues look like when examined through structural applied theory? The main reason why the study was conducted was to survey the book of Dïggʷwa there by showing the universality of St. Yared’s book of Dïggʷwa, indicating the perspective of St. Yared on social issues, and showing the level of literary development during that time. The study has been delimited to the book Dïggʷwa, specifically S'omä Dïggʷwa and examined only from the social significance perspective. The study employed qualitative research method and used non-probability sampling (critical sampling method). The main source of information was Yared’s S'omä Dïggʷwa. The study employed document analysis and used structural applied theory to do the analysis. The findings of the study showed that the book has considerable significance in terms of analyzing a number of social issues such as social cohesion, education, politics, economics, family and religion.

*ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን በፎክሎርና ሥነ ጽሑፍ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ሲኾን በቅድስት ሥላሴ ዩንቨርሲቲ ደግሞ የዶግማቲክ ቲዎሎጂ (Dogmatic Theology) የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ ናቸው። ቀሲስ ዐቢይ በማኅበረ ቅዱሳን የሐመር መጽሔት ምክትል ዋና አዘጋጅ ኾነው በማገልገል ላይ ናቸው።

## ፩ መግቢያ

ይኽ ጥናት ሦሰት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል የጥናቱ ዓይነትና ባሕርይ የተዋወቀበት ነው። ኹለተኛው የንድፈ ሐሳብና የተዛማጅ ጥናቶች ክለሳ፣ ሦስተኛው ደግሞ በጾመ ድጓ የተነገሩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ የተደረገው ትንተና የቀረበበት ነው።

### ፩.፩ የጥናቱ ዳራ

"ሥነ ጽሑፍ ከሌሎች ሙያዎች በላቀ ከሰው ልጅ ህልውና ጋራ ፍጹም የተቆራኘ ነው፤ ከማጀት እስከ አደባባይ፣ ከምድር እስከ ሰማይ አይመለከተኝም የሚለው አንድም የኑሮ ፈር፣ አንድም የሕይወት ፈርጅ የለውም" (ቴዎድሮስ፣ ፳፻፩)። ከዚህ ከቴዎድሮስ አባባል መረዳት እንደሚቻለው ሥነ ጽሑፍ የሰውን ልጅ ሕይወት በጥሬ ዕቃነት በአንድምታ የሚተረጉም የትምህርት ክፍል ነው፤ ሕይወትን ከነንዟ፣ ከነኹለመናዋ የሚያሳይ ነው። ሥነ ጽሑፍ በየዘመናቱ በራሱ ዐውድና ሥርዓት የሕይወትን ውስጣዊና ውጫዊ ምንነት ሲያሳይ ኖሯል፤ በዘመን ተሻጋሪነት ባሕርዩም ይኽንኑ ተግባሩን ይቀጥላል።

የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ ገጽታዎች ተስተውለውበታል። በርካታ ሰዎች አንድም፣ በውል በማይታወቅ መመዘኛ፣ አንድም፣ በዘመን ቅርበት ብቻ በመወሰን ዘመናዊው ሥነ ጽሑፍ በ፳ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ብቅ እንዳለ ይገልጻሉ። ይኹን እንጂ፣ ዘመን ተሻጋሪ የኾኑ ሥራዎች ለምሳሌ፣ የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶችና የኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ገድላት ኢትዮጵያ ረጅም የሥነ ጽሑፍ ታሪክ እንዳላት ያስረዳሉ። ይልቁንም ከ፲፬ኛው እስከ ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት ሥራዎች የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ወርቃማ ዘመናት ተብለው ይጠራሉ።

ሕይወትን በሥነ ጽሑፋቸው አማካይነት ከተረጐሙልን ደራስያን መካከል ቅዱስ ያሬድ ቀዳሚው ነው። ቅዱስ ያሬድ በርካታ ሥራዎችን በመሥራት ለሥነ ጽሑፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ካደረጉ ምሁራንም ቀዳሚው ነው። ከቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች መካከል አንዱ ድጓ ሲኾን በዚኽም ነገረ መለኮትን፣ ነገረ ቤተ ክርስቲያንን፣ ነገረ ቅዱሳንን፣ ነገረ ታሪክን፣ ነገረ ባህልን፣ እንዲሁም በርከት ያሉ ማኅበራዊ ጉዳዮችን እና የመሳሰሉትን ገልጾበታል። በዚኽ ጥናት የቅዱስ ያሬድን ድርሰት (በዋናነት የተጠቀመበትን) ሃይማኖታዊን ዐውድ ብቻ ሳይኾን ማኅበራዊ ፋይዳውንም በመመልከት ከሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳው አንጻር ለመመርመርና ለመተንተን ተሞክሯል። ይኽ ጥናት በቅዱስ ያሬድ

ከተደረሱት ድርሰቶች መካከል በጾም ወቅት አገልግሎቱ ጎልቶ በሚታወቀው በተለምዶ “ጾመ ድጓ” ተብሎ በሚጠራው በ“ድጓ ጾም” ማኅበራዊ ፋይዳ ላይ ያተኩራል፡፡

## ፩.፪ የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት

ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ካበረከቱ ሊቃውንት መካከል አንዱ ቅዱስ ያሬድ ነው፡፡ ይኹን እንጂ፣ ሥራዎቹ በሃይማኖታዊ ዐውድ ስለተደረሱ ሥነ ጽሑፋዊ ሚና እንዳላቸው የሥነ ጽሑፍ አካል ተደርገው አይቆጠሩም ነበር፡፡ በቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች ላይ እስከ አሁን የተካኼዱት ምርምሮች ከሃይማኖት አንጻር እንጂ ከሥነ ጽሑፍ አንጻር አይደሉም፡፡ ይኽም ከቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች መካከል አንዱ በኾነው በጾመ ድጓ ላይ በማተኮር ማኅበራዊ ፋይዳውን መመርምርና መተንተንን አስፈላጊ አድርጎታል፡፡ ጥናቱም ክፍተቱን ሙሉ በሙሉ መሙላት ባያስችልም እንኳ ለማጥበብ ግን ይረዳል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚኽ የጥናት አነሣሽ ምክንያትነት ይኽ ጥናት ተካኺዷል፡፡

## ፩.፫ የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ የጾመ ድጓን ማኅበራዊ ፋይዳ መመርመርና መተንተን ነው፡፡ ከዚህ ዋና ዓላማ የሚመነጩ ኹለት ንዑሳን ዓላማዎችም አሉት፡፡ እነርሱም በጾመ ድጓ የሚስተዋሉ ማኅበራዊ ጉዳዮችን መተንተን እና በጾመ ድጓ የተገኙትን ማኅበራዊ ፋይዳዎች ከመዋቅራዊ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ አንጻር መመርመርና መተንተን ናቸው፡፡

## ፩.፬ የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ ከቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች መካከል በአንዱ በጾመ ድጓ ላይ ብቻ የሚያተኩር ነው፡፡ ይኽ የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ ከቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች በዋናነት ጎልቶ የሚታየው ጾመ ድጓ በመኾኑ ነው፡፡ የኹሉንም የድጓ ክፍሎች በአንድ ጥናት ማካተት አስቸጋሪ በመኾኑ ከድጓ ክፍሎች መካከል በተለምዶ ጾመ ድጓ እየተባለ በሚጠራው የጾም ድጓ ማኅበራዊ ፋይዳ ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ጾመ ድጓም በልዩ ልዩ መልኩ ሊጠና ቢችልም በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገው የመጽሐፈ ጾመ ድጓን ማኅበራዊ ፋይዳ በመመርመርና በመተንተን ላይ ብቻ ነው፡፡ ጥናቱ ጾመ ድጓን ከማኅበራዊ ፋይዳው አንጻር እንጂ በውስጡ ከያዛቸው ሌሎች ጉዳዮች ማለትም፣ ከዜማ ምንነት፣ ከዜማ ታሪካዊ አመጣጥ፣ ከዜማ ምልክቶች፣ ወዘተ. አንጻር ያሉ ነገሮችን አይመለከትም፡፡

### ፩.፭ የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት በቤተ-መጻሕፍት የተወሰነ ዐይነታዊ ጥናት ነው። በዐይነታዊ ጥናትነቱም ገላጭ ምርምርን ተጠቅሟል። ገላጭ ምርምር ተመራማሪው የአንድን ጉዳይ ነባራዊ ኹኔታውን፣ ማኅበረሰባዊ ፋይዳውን፣ ችግሩን ወዘተ. የሚተነትንበት ዘዴ ነው። በገላጭ ምርምር ለሚከናወን ጥናት አመች ነው ተብሎ የሚታመነው ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ነው። የዚህ ጥናት መረጃ በሰነድ በመጽሐፍ ፍተሻ ላይ የተመሠረተ በመኾኑ የተጠቀሰውን የናሙና አወሳሰድ ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ኾኗል። በሰነድ ፍተሻ የተገኙት መረጃዎችም በቴክስቹዋል የትንተና ስልት ተንትነዋል። ጾመ ድጓን በጥልቀት በማንበብ ምን ምን ማኅበራዊ ፋይዳዎች ይኖሩታል? በሚል መሠረታዊ መነሻ ለተከናወነው ምርምር የመተንተኛ ስልቱ ቴክስቹዋል ትንተና ነው፤ ምክንያቱም ጥናቱ ከርእሱ ጀምሮ የማኅበራዊ ፋይዳ ትንተና በመጽሐፈ ድጓ የሚል ነውና ለዚህ ምርምር የተሻለ ኾኖ የተገኘው የትንተና ስልት ይኽ ስለኾነ ነው።

## ፪.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና ንድፈ ሐሳባዊ ዳሰሳ

በዚኽ ንዑስ ርእስ የመጽሐፉ ደራሲ የቅዱስ ያሬድን ማንነት፣ ለጥናቱ የተመረጠው መጽሐፍ ምንነት፣ የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት እና መጽሐፉን ለመመርመርና ለመተንተን የተጠቀምኩበት ንድፈ ሐሳብ፣ ተቃኝተዋል።

### ፪.፩ የቅዱስ ያሬድ ማንነት

ቅዱስ ያሬድ በ፭፻፭ ዓ. ም. ሚያዝያ ፭ ከአባቱ አብዩድ ከእናቱ ታውክልያ በአክሱም ከተማ ተወለደ። ቅዱስ ያሬድ አባቱ በሕፃንነቱ ስለ ሞተበት እናቱ በሃይማኖት አጽንታ፣ በምግባር ኮትኩታ እንደ አሳደገችው ጌታኹን (፳፻፲፤ ፴፰) ይገልጻሉ። ልሳነ ወርቅም (፲፱፻፺፯) ቅዱስ ያሬድ የተወለደበትን ቦታና የእናቱን ስም በተመለከተ የሰጡት መረጃ ከጌታኹን ጋራ ተመሳሳይ ነው። ይኹን እንጂ፣ ጌታኹን የቅዱስ ያሬድ አባት አብዩድ እንደ ኾነ ሲገልጹ ልሳነ ወርቅ ደግሞ አባቱ አዳም ይባላል ይላሉ። ጌታኹን ቅዱስ ያሬድ በ፭፻፭ ዓ.ም. እንደ ተወለደ ሲያስረዱ ልሳነ ወርቅ ደግሞ በ፬፻፺፫ ዓ. ም. እንደ ተወለደ ይገልጻሉ። ኹለቱ ሰዎች ቅዱስ ያሬድ የተወለደበትን ዓመት በተመለከተ የሰጡት መረጃ የተለያየ ነው።[1]

[1]አዳም ለዐቅመ ትምህርት በደረሰ ጊዜ በአክሱም ከተማ ከሊቀ ካህናት አብዩድ ብሉይና ሐዲስ ተምሮ በማዕርገ ዲቁና መቅደሰ አክሱምን እያገለገለ እያለ የመምህሩን ልጅ የጌዴዎንን ታናሽ ታውልያን አገባ። ሚያዝያ ፭ ቀን ፬፻፺፫ ዓመተ ምሕረት ዐርብ ዕለት በዘመነ ማቴዎስ ወንድ ልጅ ወለደ፤ ስሙንም ያሬድ አለው። ከዚያ በፊት ጽርሐ አርያም ወጥቶ "ከቅዱሳን መላእክት ዜማ የሚያወርድ ንብ ከየዛፉና ከየእኽሉ፣ ከየአታክልቱና ከየሣሩ አበባ ቀሥሞ ጣፋጭ ማር ሠርቶ ሰው እንዲጠቀምበት እንደሚያደርገው ኹሉ ቅዱስ ያሬድም ከብሉይ፣ ከሐዲስ፣ ከሊቃውንት፣ ከድርሳናት መጻሕፍት ኹሉ ጥሩ ጥሩ ቃላትን እየቀሠመ በዜማ አጣፍጦ ጥዑም ዜማ ለሚማሩ ሰዎች የሚያድል መቅደሰ ኢትዮጵያን እንደ ጽርሐ አርያም፣ ካህናቷን እንደ ካህናተ ሰማይ ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርን በጣዕመ ዜማ እንዲያመሰግኑ

ጥዑመ ልሳን ካሳ (፲፱፻፹፩) ስለ ቅዱስ ያሬድ ትውልድ የገለጹት የጌታኹንና የልሳነ ወርቅን ልዩነት የሚያስታርቅ ይመስላል፡፡ ቅዱስ ያሬድ በ፭፻፭ ዓ. ም. ሚያዝያ ፭ ቀን በአክሱም ከተማ ተወለደ፤ አባቱም አብዩድ ይባላል በማለት ጽፈዋል፡፡ ጥዑመ ልሳን የያሬድን አባት አዳም ያሉበትን ምክንያት ገድሉ ላይ “ተዝካረ አቡየ አዳም” በማለቱ ነው የሚል አመክንዮ አስቀምጠዋል፡፡ ይኹን እንጂ፣ “ተዝካረ አዳም” የሚለው ቃል የቅዱስ ያሬድን የሥጋ አባት ሳይኾን ቀዳማዊ አዳምን ነው፣ የሚል የሊቃውንት አነጋገር አለ፡፡ ከሊቃውንቱ አነጋገር መረዳት እንደሚቻለው አዳም የሚለው ቀዳማዊውን እንጂ የቅዱስ ያሬድን የሥጋ አባት አይደለም፡፡

ቅዱስ ያሬድ በተወለደ በሰባት ዓመቱ አባቱ አብዩድ ስለ ሞተ እናቱ ክርስቲና የአክሱም ገበዝ ለነበረው ለአጎቱ ለጌዴዎን እንዲያሳድገውና እንዲያስተምረው አደራ ብላ ሰጠችው (ጥዑመ ልሳን፣ ፲፱፻፹፩፤ ፳)፡፡ ቅዱስ ያሬድ ከአባቱ ከአብዩድ፣ ከእናቱ ክርስቲና በ፭፻፭ ዓ. ም. ተወለደ የሚለው የጥዑመ ልሳን ሐሳብ ትክክል ይመስላል፡፡ ቅዱስ ያሬድ መጀመሪያ ላይ ትምህርት አልገባው ብሎ እንደ ነበርና ከሰባት ዓመት በኋላ ግን እንደተገለጸለት በርካታ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡[2] ግንቦት ፲፩ ቀን በሚነበበው መጽሐፈ ስንክሳር ተመሳሳይ ታሪክ እናገኛለን (መጽሐፈ ስንክሳር በግእዝና በዐማርኛ ከመጋቢት እስከ ጳጕሜን፣ ፲፱፻፺፫፤ ፪፻፷፩-፪፻፷፪)፡፡

“ያሬድ” የሚለው ስም ወሪድ፣ ንህብ እና ራእየ ምስጢረ ሰማያት ተብሎ ይተረጐማል፡፡ ስሙ እንደዚህ የተተረጐመበት እና የትርጉሙ ግንኙነት ቀጥሎ የተገለጸው ነው፡፡ የአዳም ስድስተኛ ትውልድ የኾነው የሔኖክ አባት በዘመኑ በደብር ቅዱስ ይኖሩ የነበሩ ደቂቀ ሴት በቃየል ልጆች መልክ፣ ድምፅ፣ በዘፈናቸው ጣዕም ተመስጠው

የሚያደርግ ወንድ ልጅ ትወልዳላችሁ፤ ስሙንም ያሬድ ትሉታላችሁ” የሚል ትንቢት ለአባቱና ለእናቱ ይነገርላቸው ነበርና እነሆ ወንድ ልጅ ወለዱ፡፡ ስሙንም ያሬድ ብለው ጠሩት (ልሳነ ወርቅ፣ ፲፱፻፺፯፤ ፲፭)፡፡

[2] ቅዱስ ያሬድ ከአባቱ ዘንድ ገብቶ መዝሙረ ዳዊትን በሚማርበት ጊዜ ትምህርት አልገባው አለ፡፡ በዚህም ምክንያት መምህሩ ጌዴዎን ብዙ ጊዜ ስለሚቆጣውና ስለሚገርፈው ያሬድ መታገሥ ተስኖት ከወላጆቹ ቤት ወጥቶ ማይ ኪራሕ ወደምትባል ቦታ ኼዶ ተደበቀ፡፡…ያሬድ ወደ አንዲት ዛፍ ሥር ተጠግቶ ዐርፎ እያለቀሰ ሳለ አንድ ትል ዐየ፤ ትሉም ወደ ላይ እወጣለሁ እያለ ከመካከሉ ሲደርስ ይወድቅ ነበር፡፡ እንደዚህ እያለ ለ፯ ጊዜያት በተደጋጋሚ ሲወጣና ሲወርድ ከቆየ በኋላ በሰባተኛው ትሉ ከዛፉ ላይ ወጥቶ የዛፉን ፍሬ ወይም ቅጠል ሲበላ ተመለከተ፡፡ ከዚህ በኋላ ቅዱስ ያሬድ የትሉን ተስፋ አለመቁረጥ ከፍተኛ የኾነውን ጥንካሬውንና ትጋቱን እንዲሁም ወደላይ ለመውጣት ብዙ ጊዜ እየሞከረ ቢወድቅም ከዓላማው ሳይናወጥ ከብዙ ጊዜ ድካምና ጥረት በኋላ ያሰበው ኹሉ እንደ ተፈጸመለት ተመልክቶ ሰውነቱን እንዲህ ይላት ጀመር፡፡ “ሰውነቴ ሆይ! ግርፋትን ለምን አትታገሽም? መከራንስ ለምን አትቀበይም? አሁንም ትዕግሥ ትን ገንዘብ ስላላደረግሽ እግዚአብሔር ይህን ገለጠልሽ” ብሎ ዐዘነ፤ አለቀሰ፣ በመጨረሻም ወደ መምህሩ ወደ ጌዴዎን ተመለሰ፡፡ ከዚህ በኋላ በዐጭር ጊዜ መዝሙረ ዳዊትን፣ ብሉያትንና ሐዲሳትን ተማረ (ጥዑመ ልሳን፣ ፲፱፻፹፩፤ ፳)፡፡

ከደብር ቅዱስ ወደ ምድረ ፋይድ[3] በመውረዳቸው ያሬድ[4] እንደ ተባለ፣ ቅዱስ ያሬድም ሰማያዊውን ዜማ ወደዚህ ምድር ስላመጣ በዚህ ስም ተጠርቷል።

ቅዱስ ያሬድ፦ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅድስና ማዕረግ ሰጥታ፣ ቅዱስ መኾኑን ዐውጃ፣ ጽላት ቀርጻ፣ ቤተ ክርስቲያን ሰይማ "አማልደን" እያለች በየወሩ ከምታከብራቸው ቅዱሳን አንዱ ነው። በተጨማሪም ሚያዝያ ፭ የተወለደበትን፣ በግንቦት ፲፩ ደግሞ የተሰወረበትን ዓመታዊ በዓላት አድረጋ ታዘክራለች።

## ፪.፪ የድጓ ምንነት እና አከፋፈሉ

ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው የዜማ ድርሰቶች አራት ናቸው። በተለምዶ ጾመ ድጓ የሚባለው የጾም ድጓ ነው። ይኽ ከድጓ የወጣ እንጂ ራሱን የቻለ አንድ ድርሰት አይደለም። ድጓን በተመለከተ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (፲፱፻፵፰፡ ፫፻፴፰) እንዲህ ይገልጹታል።

ድጓ፦ የዜማ መጽሐፍ፣ …ድግዱግ፣ ድግዱገ ጽሕፈት፣ ጥፈቱ የከሳ የቀጠነ፣ ደቂቅ፣ ረቂቅ የኾነ፣ አሸዋ ዕብቅ ወይም ዜማ፣ ቁዘማ ግጥምና ዜማ ማለት ነው። በደገ ዘይቤ ሲፈቱት ግን ደግ ደገኛ አሰኝቶ የመጽሐፉን መጠን ታላቅነቱን ያሳያል። በርቀቱ ላይ የመንፈቅ ስንክሳር ያኽላልና። ኹለተኛም ምእላድ፣ መድበል፣ እስትጉቡእ፣ ብለው ይፈቱታል። ቃሉ ከገድል ከተአምር ከአዋልድ ሳይቀር፣ ከብሉይ ከሐዲስ ከሊቃውንት ተለቅሞ፣ ተቀስሞ የወጣ ድርሳን፣ ሕውስ፣ መዝሙር ሐዲስ ማለት ነው።

እንደ ኪዳነ ወልድ አገላለጽ ድጓ ከብዙ መጻሕፍት የተውጣጣ በርካታ ጉዳዮችና ጥልቅ ሐሳቦች የሚገኙበት ታላቅ መጽሐፍ ነው። ከቅዱስ ያሬድ በኋላ የተነሡ ሊቃውንትም የደረሱት የዜማ ድርሰት ስብስብ ነው። ዜማው አእምሮን የሚመስጥ፣ በምናብ ሌላ ዓለም ውስጥ የሚከት የኅሊና መስሕብ ነው።

በሌላ በኩል ድጓ፦

፩) ደግደገ ከሳ፣ ረቀቀ ካለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲኾን የጽሕፈቱን መርቀቅ ወይም ደቃቅ መኾን ያመለክታል፤

[3] "ምድረ ፋይድ ማለት ምድረ ኃሣር ወመርገም፣ ምድረ ድንጋፄ ወረዓድ ማለት ነው። ወአርአያ ሕሡም ወኅሱር። ክፉና መልካም፣ ቀይና ጥቁር፣ ዐጭርና ረጅም፣ ቀጭንና ወፍራም፣ ወደሚፈጠርበት። ወሲሳየ ሐዘን፤ ቢያገኙት ቁንጣን፣ ቢያጡት ቀጠና ወደሚኾንበት፣ ወፈትሐ ላዕሌሆሙ በሞት እስከ ለዝሉፉ፣ ዐምስት ሺሕ ዐምስት መቶ ዘመን እስኪፈጸም በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስን በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነምን ፈረደባቸው" (ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ፲፱፻፹፰፡፳፬)።

[4] መጻሕፍተ ብሉያት ፪ቱ እሉ እሙንቱ ኦሪት ዘፍጥረት (ዘልደቱ)፣ (ኦሪት ዘፀአት፣ ፲፱፻፺፱፡፶)።

፪) ጥቅ ማለት ነው፤

፫) ዐዲስ ዜማ ማለት ነው፤

፬) እስትጉቡእ ማለት ነው (ጌታኹን ደምፀ፣ ፳፻፲፤ ፻፬)።

መጽሐፈ ድጓ አጠቃላይ የሃይማኖት መጽሐፍ ነው። በውስጡም በሃይማኖታዊ ትምህርት የሚጠቀሱ ጉዳዮች ለምሳሌ፡- ዶግማን፣ ቀኖናን፣ ትውፊትን ያካትታል። ከዚህም በተጨማሪ ታሪክ፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ባህል፣ ሥነ ምግባር፣ ማኅበራዊ ጉዳዮች ወዘተ. ይገኙበታል። ቅዱስ ያሬድ ድጓውን ሲያዘጋጅ ከዘመናት አንጻር በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍሎታል። እነሱም፡- ዮሐንስ (ከመስከረም አንድ እስከ ኅዳር ዐምስት ያለውን ዘመን ያጠቃልላል)፣ አስተምህሮ (ከኅዳር ስድስት እስከ ዐቢይ ጾም መግቢያ ያለውን አካትቶ ይዟል)፣ ጾም (ከዘወረደ ጀምሮ እስከ ቀዳም ሥዑር ያለውን ጊዜ የሚያካትት ነው) እና ፋሲካ (ከትንሣኤ ጀምሮ እስከ ጳጉሜን ዐምስት ወይም ስድስት ያለውን ያካትታል) ናቸው። ዘመናቱ በያንዳንዳቸው ሥር የሚካተቱ ንኡሳን ዘመናትን ሳይጨምሩ በዋናነት እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

ጾመ ድጓ ከዐራቱ የድጓ ክፍሎች መካከል አንዱ እንደ ኾነ ከላይ ተጠቅሷል። ይህ ክፍል ብቻውን ተዘጋጅቶ ጾመ ድጓ በሚል ስያሜ የሚታወቀው ነው። መጽሐፉ ስምንት ክፍሎች ያሉት ሲኾን እነርሱም ዘወረደ፣ ቅድስት፣ ምኵራብ፣ መጻጕዕ፣ ደብረ ዘይት፣ ገብር ኄር፣ ኒቆዲሞስና ሆሳዕና ናቸው። የአከፋፈል ኹኔታው ሳምንትን መሠረት ያደረገ ነው። የሳምንቱ ስያሜና በየሳምንቱ የሚነሡ ጉዳዮችም፡-

ዘወረደ፡- በመጀመሪያው ሳምንት የሚታሰብ ሲኾን ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ዓለምን ማዳኑን የሚመለከቱ ጉዳዮች የሚነገሩበት ነው።

ቅድስት፡- የኹለተኛው ሳምንት የሚታሰብበት ሲኾን የሰንበትን ቅድስትነት የሰው ልጅ በአግባቡ ማክበር እንዳለበት፣ ሰንበት ስለ ሰው ልጅ እንደ ተፈጠረች እንዲሁ የሰውን ልጅም ክቡርነትና ቅድስና ይናገራል።

ምኵራብ፡- ሦስተኛው ሳምንት የሚታሰብበት ሲኾን ቤተ መቅደሱን የንግድ ቤት ያደረጉትን እንደ ወቀሣቸው፣ መውቀሥ ብቻ ሳይኾን በጅራፍ እየገረፈ እንዳስወጣቸው፣ “ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል እንጂ የንግድ ቤት ሊኾን አይገባም” ብሎ ያስተማረውን ትምህርት ያስረዳል።

መፃጉዕ፡- ይህ ዐራተኛው ሳምንት የሚታሰብበት ሲኾን በሽተኞችን ማለትም መጻጕዕን፣ ዐይነ ስውሩንና ሌሎችንም በሽተኞች እንደ ፈወሰ ያስረዳል፡፡

ደብረ ዘይት፡- ይህ ዐምስተኛው ሳምንት የሚታሰብበት ሲኾን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ያስተማረው ትምህርት ይዘከርበታል፡፡ በዚህ ትምህርትም ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ እንደሚመጣ፣ በኃጥአን እንደሚፈርድባቸው፣ ለጻድቃን ደግሞ እንደሚፈርድላቸው ይናገራል፡፡

ገብር ኄር፡-ይኽ ስድስተኛው ሳምንት የሚታሰብበት ሲኾን ስለ ታማኝ አገልጋዮችና ስለማይታመን አገልጋይ ይናገራል፤ በዚኽም የንግድና የጠንካራ ሥራ ባሕል ይገኝበታል፡፡

ኒቆዲሞስ፡- ይህ ሰባተኛው ሳምንት የሚታሰብበት ሲኾን ኒቆዲሞስ የተባለ የአይሁድ መምህር ሌሊት ሌሊት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እየሄደ ይማር እንደ ነበረ ያስተምራል፡፡

ሆሳዕና፡- ይህ ስምንተኛው ሳምንት የሚታሰብበት ሲኾን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ "ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ ምስጋና ይገባል" እያሉ ሕዝቡ በደስታ፣ በአክብሮትና በምስጋና እንደ ተቀበሉት ያስረዳል፡፡

## ፪.፫ የተዛማጅ ጽሑፎች ክለሳ

ቅዱስ ያሬድንም ኾነ የቅዱስ ያሬድን ሥራዎች ከሀገራዊ አስተዋፅኦ አንጻር የመረመሩ ጥቂት ሥራዎችን እናገኛለን፡፡ የተወሰኑት መጽሐፈ ድጓን በልዩ ልዩ መልኩ መርምረው ለአንባቢያን አቅርበዋል፡፡ ከእነዚኽም መካከል አንዱ ድጓ ላይ ብቻ የሚያተኩር ሲኾን ሌሎቹ ደግሞ በአጠቃላይ በቅዱስ ያሬድ ሥራዎች ላይ ያተኩራሉ፡፡ በቅድሚያ ጌታኹን ደምፀ (፳፻፲) በመጽሐፈ ድጓ ላይ ያካኼዱትን ጥናት እንቃኛለን፡፡ ጌታኹን በጥናታቸው የመዝሙርን ምንነት፣ አጀማመርና መስስፋፋት፣ የዜማን ምንነት እና መሰል ጉዳዮችን መርምረዋል፡፡ የድጓን ምንነት፣ የዜማን ምልክቶች፣ የዜማን ስልቶች፣ የድጓውን አከፋፈል ከነምሳሌው፣ የቅዱስ ያሬድን እድገት፣ የትምህርት ሕይወት፣ ያሬድ በሥራው ከሌሎች የሙያ መስኮች ጋራ ያለውን ግንኙነት ወዘተ. አጥንተዋል፡፡

የእኔ ጥናት፣ የጌታኹን ጥናት ትኩረት ካደረገባቸው የድጓ ክፍሎች ውስጥ በአንዱ በጾመ ድጓ ላይ ማተኮሩ ያመሳስላቸዋል፡፡ በሌላ በኩል፣ የእኔ ጥናት የመጽሐፉን ማኅበራዊ ፋይዳ በጥልቀት ሲመረምር የጌታኹን ደግሞ ሃይማኖታዊ ዐውዱ ላይ ይበልጥ ትኩረት በመስጠቱ ከእኔ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡ የጌታኹን ጥናት አጠቃላይ ድጓ ላይ ሲያተኩር የእኔ ጥናት ደግሞ በጾም ወቅት አገልግሎት በሚሰጠው በጾመ ድጓ ላይ ብቻ ማተኮሩ የኹለቱ ጥናቶች ተጨማሪ ልዩነት ነው፡፡ የእኔ ጥናት የጥናቱን

አስፈላጊነት፣ አነሣሽ ምክንያት፣ የጥናቱን ዘዴ፣ የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት፣ ጥናቱ የተጠቀመበትን ንድፈ ሐሳብ ዓይነት ወዘተ. መግለጹ ከኔታኹን የተለየ ያደርገዋል።

ቀጥለን ደግሞ በተወሰነ መልኩ ከድጓ ጋራ ግንኙነት ያለውን የሥርግው ገላውን (፳፻፱) ጥናት እንቃኛለን። የሥርግው ጥናት ዓላማ የግእዝ ቅኔ እድገት ምን እንደሚመስል መግለጥ ነው። መረጃዎችን የሰበሰቡት በመዛግብት ፍተሻ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ ወዘተ. ሲኾን የመረጃ መተንተኛ ዘዴያቸው ንጽጽራዊ ዘዴ ነው። የስርግው ጥናት ትኩረት በግእዝ የቅኔ እድገት ላይ ይኹን እንጂ፣የቅዱስ ያሬድን ታሪክ፣ የድጓ ደራሲነት፣ ድጓ የተደረሰበትን ዘመን፣ የድጓን ይዘት፣ የድጓ ድርሰትን ምንጭ፣ ድጓ በዘመናት ያሳየውን እድገት፣ የድጓን የዜማ ስልት፣ የድጓን አርእስት፣ የድጓን የቅኔ መሠረትነት፣ ድጓ ለቅኔ እድገት ያለውን አስተዋፅኦ እንዲሁም አሁን ላይ ድጓ በልዩ ልዩ ቦታዎች የተለያዩ ዜማዎች (ቤተ ልሔም፣ ቆሜ፣ አጫብር፣ ተጕለት፣ ዋድሌ ወዘተ.) በመባል መከፈሉን ቃኝተዋል። የስርግው ጥናት በድጓ ላይ መኾኑ፣ ስለ ያሬድ ማንነትና እድገት፣ ስለ ዜማ ስልቶችና ዓይነቶች፣ ስለ ድጓ እድገት በመመርመሩ ከእኔ ጥናት የተለየ ያደርገዋል። ሥርግው የመረመሩት ኹሉንም የድጓ ክፍሎች ሲኾን የእኔ ጥናት ግን የድጓ ክፍል በኾነው በጾመ ድጓ ላይ ብቻ በመወሰኑ ከእሳቸው ጥናት ይለያል። የስርግው ጥናት በዋናነት ድጓን ከቅኔ እድገት አንጻር ያለውን ፋይዳ መርምሯል። በተጨማሪም የእኔ ጥናት ትኩረቱ በድጓ የተነገረውን ማኅበራዊ ፋይዳ ማጥናት በመኾኑ ከሥርግው ይለያል።

ራልፍ ሊ (፳፻፲፩) ለሦስተኛ ዲግሪ ያዘጋጁት የመመረቂያ ጥናት ዓላማ በኢትዮጵያና በኤፍሬማውያን[5] መካከል ያለውን የውክልና ስልት በንጽጽር መልክ ማሳየት ነው። ጥናቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና የአይሁድ እምነት ባህል እንደሚንጸባረቅበት ያስረዳል። ይሕ ጽሑፍ የኢትዮጵያንና የኤፍሬማውያንን የሥነ ጽሑፍ ምንጮች ይገልጻል። መጽሐፈ ድጓ ይዘቱ የክብረ በዐላት፣ የዘወትር፣ የወርኀ ክረምት፣ የወርኀ ጽጌ፣ የጾም፣ የሰንበት፣ የበጋ ወዘተ. ወቅቶችን ኹሉ እንደሚመለከት ያስረዳል። መጽሐፈ ድጓ ሀገር በቀል እንጂ ትርጉም ወይም ውርስ መጽሐፍ እንዳልኾነ ይናገራል። የድጓ መሠረቱ ቅዱስ ያሬድ ቢኾንም መሠረታዊ ይዘቱ ሳይለወጥ በአባ ጊዮጊስ ዘጋሥጫ እንደ ተከለሰም ራልፍ ይናገራል።

መጽሐፉ በብሉይ ኪዳን የተነገሩት ምሳሌዎች በሐዲስ ኪዳን አማናዊ ትርጕማቸው ምን እንደሚመስል ከብሉይ ኪዳን እያጣቀሰ ቅዱስ ያሬድም ቅዱስ ኤፍሬምም እንደ ተረጕሙት ይገልጻል። በዚኽም በብሉይ ኪዳን የተነገሩት ምሳሌዎች ለሐዲስ ኪዳኗ

[5] ኤፍሬማውያን ማለት ውዳሴ ማርያምን የደረሰው ቅዱስ ኤፍሬምን የሚከተሉትና በርሱ አስተምህሮ የሚመሩት የቅዱስ ኤፍሬም ተከታዮች የሚጠሩበት ስም ነው።

ቤተ ክርስቲያን፣ ቅድስት ድንግል ማርያም፣ ቅዱስ መስቀል፣ ጥምቀት እና እነዚህን ኹሉ አማናዊ ያደርግ ዘንድ ወደዚህ ዓለም የመጣው የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ እንደ ኾኑ ያስረዳል።

የራልፍ ሊ (፳፻፲፩) ጥናት የድጓ ደራሲ ቅዱስ ያሬድ መኾኑንና ከእርሱ በኋላ የተነሡ ሊቃውንት እንዳስፋፉት መግለጹ ከእኔ ጥናት ጋራ ያመሳስለዋል። የራልፍ ሊ ጥናት አጠቃልሎ፣ ምስጋና፣ ምኅጻረ ቃል፣ ማውጫና መግቢያ ቢኖረውም የጥናቱን ዓላማ፣ የጥናቱን አነሣሽ ምክንያት፣ የጥናቱን ገደብ፣ የጥናቱን አስፈላጊነት፣ የጥናቱን ዘዴ ወዘተ. አለመግለጹ ከዚኽ ጥናት የተለየ ያደርገዋል። የራልፍ ሊ (፳፻፲፩) ጥናት በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የሚስተዋል ውክልናዊ ትርጉም ላይ ማተኮሩ ማኅበራዊ ፋይዳን ከሚመረምረው ከእኔ ጥናት የሚለይበት ሌላው ነጥብ ነው። እንዲሁ የራልፍ ሊ ጥናት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውክልናዊ አገላለጽን ከኤፍሬማውያን ጋራ የሚያነጻጽር ሲኾን የእኔ ግን የቅዱስ ያሬድ ሥራዎች ከኾኑት የአንዱን የጾመ ድጓን ማኅበራዊ ፋይዳ ማሳየት ነው።

ድጓን በተመለከተ ከተካኼዱት ጥናቶች አንዱ ሰንኮሪስ አያሌው (፳፻፰) ለኹለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያካኼዱት ጥናት ነው። የሰንኮሪስ ጥናት በቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት የዜማ ምልክቶች፣ ታሪክ፣ አተገባበርና ትርጉም ላይ ያተኩራል። የእርሳቸው ጥናት ዓላማ እያንዳንዱን የዜማ ምልክት በማጥናት ከቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት አንጻር በቍጥር ማስላትና የግእዝ፣ የዐማርኛ፣ የግእዝና የዐማርኛ የሚሉትን መመደብ ነው። ምርምራቸው ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ሲኾን የመተንተኛ ስልታቸውም ገለጻ ነው። ሰንኮሪስ በጥናታቸው የዜማን አጀማመርና እድገት፣ የዜማ ጀማሪ ቅዱስ ያሬድ መኾኑን፣ ከቅዱስ ያሬድ በኋላ የተነሡ ሊቃውንት እንዳስፋፉት፣ የዜማን ምልክት አጀማመርና እድገት፣ የዜማን ምልክት በማስፋፋት ከቅዱስ ያሬድ በኋላ የተነሡ ሊቃውንት የነበራቸውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ፣ ይህም በዋነኛነት በ፲፮ኛው ክ/ዘመን እንደ ኾነ በዚህ ደግሞ አዛዥ ጌራና አዛዥ ራጉኤል ከፍተኛ ድርሻ እንደ ነበራቸው፣ ምልክቶች ከግእዝም ከዐማርኛም የተወሰዱ እንደ ኾኑ ማለትም የግእዝም የዐማርኛም ቃላት ጥምር የኾኑም እንዳሉ በጥናታቸው አስረድተዋል። ሰንኮሪስ በማጠቃለያቸው የዜማ ምልክቶቹ የመማር ማስተማር ኺደቱን ከመምህራንም ኾነ ከተማሪዎች አንጻር እጅግ ቀላል እንደሚያደርጉት፣ የዜማ ምልክቶቹ በምኅጻረ ቃል መቀመጥ ኢትዮጵያ ዛሬ ላለው ዓለም ዐቀፋዊ ውክልና ለምሳሌ በኬሚስትሪ፣ በፊዚክስ፣ በሳይኮሎጂ ወዘተ. ዓለም ለሚግባባቸው ውክልናዎች በመነሻነት ከሚጠቀሱት ሀገራት ያስመድባታል፤ ይኽም ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ልዩ የምትኾንበት መኾኑን አስረድቷል።

እኔም፣ ሰንኮሪስም ዐይነታዊ ምርምር ላይ ማተኮራችን፣ በዐይነታዊ ምርምር የሚካተተውን ገላጭ ምርምር መጠቀማችን፣ በሰነድ ፍተሻ መረጃዎችን መሰብሰባችን የጥናቶቻችንን ሥነ ዘዴ ያመሳስለዋል። በሌላ በኩል፣ የሰንኮሪስ ጥናት የቅዱስ ያሬድ ሥራዎችን ኹሉንም የመረመረ ሲኾን የእኔ ግን በጾመ ድጓ ላይ ብቻ የሚያተኩር መኾኑ ልዩ ያደርገናል። በተጨማሪም የሰንኮሪስ ጥናት በዜማ ምልክቶች ታሪክ አተገባበርና አተረጓጐም ላይ ማተኮሩ የእኔ ጥናት ደግሞ ጾመ ድጓን ከማኅበራዊ ፋይዳው አንጻር መመርመሩና መተንተኑ ከእኔ ጥናት ይለያል።

በዚኽ ጥናት የተቃኙት ኹሉም ተዛማጅ ጽሑፎች የጾመ ድጓን ማኅበራዊ ፋይዳ ባለመመርመራቸው የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት ይኽን ጥናት ማካኼድ አስፈላጊ ኾኗል። ከዚኽ ቀጥሎ የጾመ ድጓ ማኅበራዊ ፋይዳን እንተነትናለን።

## ፫. መረጃ ትንተና

በዚህ ንኡስ ርእስ ከጾመ ድጓ በንባብ የተገኙ መረጃዎች ይተነተናሉ። የዚኽ ጥናት ዋነኛ ትኩረት በጾመ ድጓ የተገለጸውን ማኅበራዊ ፋይዳ መመርምርና መተንተን ነው። በማኅበራዊ ሳይንስ የሚከናወኑ ጥናቶች ማእከላቸው የሰው ልጅ ነው። በሃይማኖትም ከማንኛውም ፍጥረት ይልቅ የሰው ልጅ ክብር ያለው፣ ኹሉም ፍጥረታት ለሰው ልጅ ሲባል የተፈጠሩ እንደ ኾኑ በሰፊው ይነገራል። "እስመ በእንተ ሰብእ ገብረ ኵሎ፤ ኹሉንም ስለ ሰው ሲል ፈጠረው" እንዲል (እዝራ፣፳፻፰፡፬፡፳)። የቅዱስ ያሬድ መጽሐፍ ዋናውና ማእከሉ የሰው ልጅ ስለመኾኑ፡- "ሰንበት ይእቲ፤ ቅደስት ይእቲ፤ ሰንበት ተዐቢ እምኵሉ ዕለት፤ እስመ ሰንበትሰ በእንተ ሰብእ ተፈጥረት። ሰንበተ ሰንበታቲሁ ለውሉደ ሰብእ መድኃኒት፤…" ("ሰንበት የተቀደሰችና የተለየች ናት፤ ከዕለታት ሁሉ ሰንበት ትበልጣለች፤ ሰንበት ስለሰው ተፈጥራለችና። የሰንበታት ኹሉ ሰንበት ለሰው ልጅ መድኃኒት ናት፤…") (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፡፴፱) እንዲል።

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው ጾመ ድጓን ከማኅበራዊ ፋይዳ አንጻር መመልከት ሰውን ማእከል ማድረግ ነው። ፍጥረት ኹሉ ለሰው ተፈጥሯል፤ ሰንበትም ለሰው ተፈጥሯል፤ እንስሳቱ ለሰው ተፈጥረዋል፤ አራዊቱም ቢኾኑ ለሰው ተፈጥረዋል።

ማኅበራዊ ፋይዳ በአንድ ማኅበረ ሰብ ውስጥ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ የሚዘወተሩትን በማኅበረሰብ መካከል ትስስር መፍጠር የሚችሉትን ጉዳዮች የሚመለከት ነው። በዚህም አንድ ጉዳይ ለአንድ ማኅበረሰብ ያለው ፋይዳ ምን ይመስላል? የሚለውን ይመለከታል። ፋይዳውንም በዋናነት በማኅበረሰቡ ሕይወት ላይ ከሚስተዋሉት ጉዳዮችና ለማኅበረሰቡ ከሚፈጥሩት ትስስር አንጻር መመልከት ይቻላል። እነዚህ ጉዳዮች ማኅበራዊ ትስስር፣

ፖለቲካ፣ ትምህርት፣ ምጣኔ ሀብትና ሃይማኖት ተጠቃሾች ናቸው። በመኾኑም መጽሐፈ ጾመ ድጓ እነዚህን ጉዳዮች ከመመልከት አንጻር ምን ፋይዳ አለው? የሚለው የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ነው።

## ጾመ ድጓ ማኅበራዊ ትስስርን ከመፍጠር አንጻር

ማኅበራዊ ትስስር ማለት ሰው አንዱ ከሌላው ጋራ የሚያደርገው ግንኙነት ነው። ሰው ማኅበራዊነትን የሚሻ ብቻውን ከመኖር ይልቅ አብሮ መኖር የሚመቸው ፍጥረት ነው። በሥነ ፍጥረት ታሪክ አዳም ብቻውን ለአንድ ሳምንት ያህል እንደ ሰነበተ፣ በዚህ ጊዜ ግን በብቸኝነቱ እጅግ እንዳዘነ ተመዝግቧል።[6] ስለዚህ ሰው አብሮነትን የሚሻ ማንም ቢኾን በራሱ ምሉዕ ያልኾነ የርስ በርስ ትስስር የሚያስፈልገው እንደ ኾነ ያስረዳል። ቅዱስ ያሬድ በመጽሐፈ ድጓ ለሰው ልጅ እንዲህ ያለውን ወሳኝ ጉዳይ እንዴት ቃኝቶታል የሚለው የዚህ ጥናት ትኩረት በመኾኑ ቀጥለን እንመለከተዋለን።

## የጸሎት ሥርዐት

ማኅበራዊ ትስስር በብዙ መልኩ ይፈጠራል፤ በዚህ ንኡስ ርእስ ማኅበራዊ ትስስር ከሚፈጠርባቸው ነገሮች መሀል የጸሎትን ሥርዐት እንመለከታለን። መጽሐፉ በማኅበር የሚባል፣ በመጽሐፉ ውስጥ ከተካተተው ይዘት በተጨማሪ ራሱ ቅዱስ ያሬድ የደረሰው "ዘይነግሥ" የሚባል ጸሎት እንዲጸለይ ያዝዛል። ጸሎቱም ስለ ልዩ ልዩ አካላት የሚጸለይ በመኾኑ ማኅበራዊ ትስስርን ያጠነክራል። ሥርዐተ ጸሎቱ ኅብረትን በሚያበረታታ መንፈስ የተዘጋጀ በመኾኑ ማኅበራዊ ትስስርን ያጠናክራል።

ይህ መጽሐፍ በሚጸለይበት ጊዜ መላ መጽሐፉ ምስጋና፣ ጸሎት፣ ትምህርት እንደ ኾነ ኹሉ በየመኻሉ ስለ ልዩ ልዩ አካላት እንዲጸለዩ ያዝዛል። ለምሳሌ፡- መንግሥቱ (፳፻፱) ገጽ ፱፣ ፲ እና ፳፪ ላይ በስደት ስላሉት፣ ገጽ ፱፣ ፳፪ እና ፪፻፪ ስለ ዝናማት፣ ገጽ ፱ እና ፳፪ ስለ ንጉሥ፣ ገጽ ፲ ስለ ታመሙት ወዘተ. ጸሎት እንዲደረግ ያዝዛል። ይህ በየምዕራፉ ወይም በየመሐሉ ስለ ተሰደዱ ሰዎች፣ ስለ ታመሙ ሰዎች፣ ስለ ሀገሪቱ ንጉሥ፣ ስለ ዝናማት ወዘተ. ኹሉ እንዲጸለይ የሚያዝዘው ነገር ምን ያህል የርስ በርስ

[6] ለአዳም ግን እንደርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር። ጌታ ዐርብ በነግህ አዳምን ፈጥሮ፣ ቅዳሜ መፍጠሩን ተወ፤ እሑድ እንስሳትን አራዊትን አመጣለት፤ ስም አወጣላቸው። ሰኞ ማክሰኞ አዕዋፍን አመጣለት፤ ስም አወጣላቸው። ረቡዕ በየብስ የተፈጠሩ ፍጥረታትን አመጣለት፤ ስም አወጣላቸው። ኀሙስ በባሕር የተፈጠሩ ፍጥረታትን አመጣለት፤ ስም አወጣላቸው። ተባዕትና እንስት ኹነው ዐይቶ ከእኔ በቀር ብቻውን የተፈጠረ የለም ብሎ ዐዘነ፤ በዚህ ጊዜ ጌታ "ኢኮነ ሠናየ ለእጓለ እመሕያው ይንበር ባሕቲቶ" ብሎ "ንግበር ቢጸ ዘትረድኦ" አለ። (መጻሕፍተ ብሉያት ፩ቱ እሉ እሙንቱ ኦሪት ዘፍጥረት (ዘልደቱ)፣ ኦሪት ዘፀአት፣ አንድምታ ትርጓሜው፣ ፲፱፻፺፱፤ ፳፯)።

*መተሳሰብን፣ አንዱ ለሌላው መጸለይ የሚገባ መኾኑን፣ ማኅበራዊ ትስስርን ከመፍጠር አንጻር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው መኾኑን እንድንረዳ ያደርገናል።*

ከዚህም በተጨማሪ በሆሳዕና ሳምንት ከእሑድ ጧት ቅዳሴ ውጭ ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ማታ ድረስ የተለየ የጸሎት ሥርዐት ይከናወናል። ከሌላው የጾመ ኢየሱስ ሳምንታት በተለየ ኹኔታ አማኞች ወደ ቤተ ክርስርቲያን እየኼዱ በጋራ የሚሰግዱበት፣ የሚጸልዩበት፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕማምና መከራ፣ የሰው ልጅ ለ፶፻፭፻ ዘመናት ያኽል በመከራና በሥቃይ መቆየቱን የሚያስታውሱ ምንባባትና የጸሎት ክፍሎች እየተመረጡ በየሰዓቱም ቅዱስ ያሬድ የደረሰው የድጓ ክፍል በዜማ እየተዜመ የሚከናወንበት ሥርዐት ነው። ይኽን ኹሉ ስንመለከት መጽሐፉ ማኅበራዊ ትስስርን ከመፍጠር አንጻር ከፍተኛ አበርክቶ እንዳለው እንገነዘባለን።

### ርስ በርስ መረዳዳትና መፈቃቀር

በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የርስ በርስ ትስስር አለ ከተባለ በዋናነት የሚከተሉት ጉዳዮች በጥቂቱ ተሟልተዋል ማለት ነው። ለምሳሌ፦ ይቅር ማለት፣ አንዱ ለሌላው ማሰብ፣ አንዱ ለሌላው መመጽወት፣ ርስ በርስ መፈቃቀር ወዘተ. ናቸው። ይህን በተመለከተ ቅዱስ ያሬድ "ሶበ ትዜክር አበሳሁ ለእኁከ ዘገብረ ለከ ተንሢአከ ጸሊ ሰፊሐከ እዴከ በጥቡዕ ልብከ አስተሥሪ ሎቱ ኀበ እግዚአብሔር ተዘኪረከ ዘይቤ መድኀኒነ ኩኑ ኄራነ ወኩኑ መጽዋትያነ" ("ባልንጀራህ በአንተ ላይ ያደረገውን በደል ባሰብህ ጊዜ ተነሥተህ በቁርጥ ልቡና ኾነህ እጅህን ዘርግተህ ጸልይለት፤ መድኃኒታችን ቸር ኹኑ መጽዋችም ኹኑ ያለውን አስበህ ወደ እግዚአብሔርም ይቅር በልለት") (መንግሥቱ፣ ፳፻፬፤፳፩)።

በዚህ ምንባብ "ወደ እግዚአብሔርም ይቅር በልለት" መልካም ውለታ የዋለልህን፣ ጥሩ ነገር ያደረገልህን ወዳጅኽን አይደለም። ይልቁንም የበደለኽን ሰው ባሰብኽ ጊዜ ተነሥተኽ ስለ ርሱ ጸልይ፣ ወደ እግዚአብሔርም ለምንለት። ራሩ የሚለውንም የእግዚአብሔርን ቃል በማሰብ ርኅሩኅ ኹን፤እያለ በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባውን መልካም ትስስር፣ የርስ በርስ መረዳዳት ከመጽሐፍ ቅዱስ "የሚራሩ ብፁዐን ናቸው፤ እነርሱ ምሕረትን ያገኛሉና" (ማቴ. ፭፣ ፯)[7] የሚለውን ጠቅሶ ያስረዳል። ይህ ለሰው ራሩ፤ ለሰው ፍቅር ይኑራችሁ፤ ርስ በርሳችሁ ተሳሰቡ የሚለው ግብረ ገብነትን፣ የርስ በርስ ማኅበራዊ ትስስርን የመፍጠሪያ መንገድ መኾኑን እንረዳለን። መከባበርና፣

---

[7] "ምሕረት ሥጋዊ፣ ምሕረት መንፈሳዊ፣ ምሕረት ነፍሳዊ አለ፤ ምሕረት ሥጋዊ ቀዶ ማልበስ፣ ቆርሶ ማጉረስ ቢበድሉ ማሩኝታ ቢበደሉ ይቅርታ ነው። ምሕረት መንፈሳዊ፣ ክፉው ምግባር በጎ ምግባር መስሎት ይዞት ሲኖር መክሮ፣ አስተምሮ ክፉውን ምግባር አስትቶ በጎውን ምግባር ማሠራት ነው፤ ምሕረት ነፍሳዊ፣ ክፉው ሃይማኖት በጎ ሃይማኖት መስሎት ይዞት ሲኖር ክፉውን ሃይማኖት አስትቶ በጎውን ሃይማኖት ማስያዝ ነው" (ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ፲፱፻፹፰፤ ፻፱)።

መፈ.ቃቀር ምን ያኽል አስፈላጊና ለሰው ኹሉ ጠቃሚ መኾኑን ቅዱስ ያሬድ ያስረዳል። “ሰንበተ አክብሩ፤ ሠናየ ግበሩ፤ ቢጸክሙ አፍቅሩ፤ እስመ ዘአፍቀረ ቢጾ ይነሥእ ዕሴቶ እምኀበ አብ እምሰማይ፤ ሰንበትን አክብሩ፤ መልካምንም አድርጉ፤ ባልንጀራችሁን ውደዱ፤ ባልንጀራውን የሚወድ ኹሉ ዋጋውን ከሰማይ ከአብ ይቀበላልና” (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤፩)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ከማኅበራዊ ትስስር ጋራ የሚገናኙ ቢያንስ ኹለት ነገሮችን እናገኛለን። እነርሱም መልካም ማድረግ እንደሚገባና ባልንጀራን መውደድ እንደሚገባ የሚሉ ናቸው።

## ትምህርት

ትምህርት፡- “መሀረ” ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲኾን ትርጉሙም መማር፣ መምህር መኾን፣ መምራት፣ ማሳየት፣ መምከር፣ ማስተማር፣ ማልመድ፣ ማስለመድ፣ መቅጣት፣ መግረፍ፣ መቈጣት፣ መዝለፍ ማለት ነው (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ ፲፱፻፹፰፤ ፫፻፸፱)። ትምህርት ጠባብ እና ሰፊ ትርጉሞች አሉት። የትምህርት ጠባብ ትርጉም ትምህርት ማለት በትምህርት ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚሰጠው ብቻ እንደ ኾነ ከዚህ ውጭ የሚገኘው ማንኛውም ዕውቀትም ኾነ ተሞክሮ ትምህርት እንዳልኾነ የሚናገሩለት ነው። በእነዚህ ዐውዶች ውስጥ የትምህርት ዓላማዎች የሚለኩት በዲግሪዎች ወይም በዕውቅና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች ነው። ይህ ዓይነቱ ትምህርት አስተማሪው የተማረውን/ያወቀውን ለሌሎች በማሳወቅ ለምሳሌ፦ እንደ መሐንዲስ፣ ዶክተር፣ መምህር፣ ነጋዴ እና የመሳሰሉ የሙያ ሰዎችን ለማፍራት ያለመ ነው (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ ፲፱፻፹፰፤ ፫፻፸፱)።

የትምህርትን ትርጉም በሰፊው ስንመለከተው ደግሞ ትምህርት በክፍል ወይም በትምህርት ቤት ብቻ የተወሰነ አይደለም። አንድ ግለሰብ በተለያዩ የሕይወት መስኮች (በመደበኛ፣መደበኛ ባልኾነና በተለያዩ አጋጣሚዎች) የሚያገኛቸውን ልምዶች፣ ዕውቀቶች እና ጥበባት የሚያካትት፣ የዕድሜ ልክ ሂደት እንደ ኾነ ይቈጠራል። ሰፊው ዕይታ ትምህርትን በግለሰብ ሰብእና ላይ የመቅረጽ ወይም የመደመር ውጤት ያለው ድርጊት ወይም ተሞክሮ አድርጎ ይቈጥረዋል። ትምህርት የማኅበራዊ ለውጥ መሣሪያ ብቻ ሳይኾን፣ በሀገር ልማት ውስጥ መዋዕለ ንዋይ መኾኑ ይታመናል። ትምህርት በትምህርት ቤት ወይም በቤት፣ በማኅበረሰቡ እና በኅብረተሰቡ ውስጥ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች እና መስተጋብሮች ውስጥ የሚቀበላቸውን ኹሉንም ልምዶች ያካተተ የዕድሜ ልክ ሂደት እንደ ኾነ ይቈጠራል (ብሔራዊ የትምህርታዊ ምርምር እና ሥልጠና ምክር ቤት/NCERT, ፳፻፲፬፡ ፮)።

ከላይ ከተገለጹት ኹለት ፅንሰ ሐሳቦች ትምህርት በመደበኛም፣ በኢመደበኛም የሚገኝ እንደ ኾነ ተረድተናል። በዚሁ መሠረት የቅዱስ ያሬድ መጽሐፈ ጾመ ድጓ፣ ማኅበረሰብ የሚገነባበትን ወይም ማኅበራዊ ፋይዳ ሲኖሣ በጀርባ አጥንትነት የሚጠቀሰውን የትምህርትን አስፈላጊነት ከመግለጽ አንጻር፤ በመደበኛም ኾነ በኢመደበኛ መልኩ የሚገኝ እንደ ኾነ ከማስረዳት አንጻር፣ "እንዴት ተመልክቶታል?" የሚለውን ቀጥለን እንመለከታለን።

### የትምህርት ምንነትና አስፈላጊነት በጾመ ድጓ

"ኵሎ እንከ ከመ ብእሲ ጠቢብ ዘይጸውም ወይጼሊ ወያስተሰሪ በእንተ ኀጢአቱ፤ ሑሩ በጽድቅ ትርከቡ ሠናየ፤ አክብሩ ሰንበተ፤ ተመሀሩ ገቢረ ሠናይ፤ ሑሩ በጽድቅ ትርከቡ ሠናየ፤ ሑሩ በጽድቅ ትርከቡ ሠናየ)" ("እንግዲህ ስለ ኃጢአቱ እንደሚጸልይና እንደሚጾም እንደ ጠቢብ ሰው ኹሉ፤ መልካምን ታገኙ ዘንድ በእውነት ኑሩ" (፫ ጊዜ) (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤፩)።

በዚህ ምንባብ ቅዱስ ያሬድ አስቀድሞ እንደ ጥበበኛ ሰዎች ኹሉ ይለናል። ይህን ካለን በኋላ ጥበበኛው ጥበበኛ የተባለበትን ምክንያት ሲያስረዳ የሚጾም፣ የሚጸልይና ስለ ኀጢአቱ የሚጸጸት ሰው ብሎ አስቀድሞ ጥበበኛ መኾን እንዳለብን ከዚያም በበጎ ምግባር መኖር እንዳለብን ያስረዳል። ትምህርት ጥበብን መፈለግ፣ ለጥበብ መትጋት፣ የጥበብ ሰው መኾንና መልካም ነገርን መሥራት ነው። ስለዚህ ጥበበኛ ኹኑ በማለት በሚያስተላልፈው መልእክት የትምህርትን አስፈላጊነት፡- "ሚጠኒ እግዚኦ እምስሕተት ውስተ አእምሮ ዚአከ ከመ እሕየው ወዕቀብ ነቢበከ ወአለብወኒ እትመሀር ትእዛዘከ፤ ሚጠኒ እግዚኦ በኂሩትከ። ዘሜጥኮ ለጳውሎስ እንዘ ሰዳዲ ውእቱ ወለፈያታዊ ኀረይኮ በቅጽበት፤... ለመጸብሐዊ ዘረሰይኮ ወንጌላዌ ከመ ይኩን ድርገተ እንተ ላዕለ ኀይል..." ("ሕግህን እንድጠብቅና እንድድን ከስሕትት አንተን ወደ ማወቅ መልሰኝ፤ ትእዛዝህን እማር ዘንድ ማስተዋሉን ስጠኝ፤ አቤቱ በቸርነትህ መልሰኝ። አሳዳጅ የነበረውን ጳውሎስን የመለስኸው፣ ወንበዴውንም በቅጽበት የመረጥኸው አቤቱ እኔንም በቸርነትህ መልሰኝ፤ ቀራጩ ማቴዎስን ኃይል መንፈሳዊን ይጎናጸፍ ዘንድ ከቀራጭነት ወደ ወንጌላዊነት የመለስኸው አቤቱ በቸርነትህ መልሰኝ...") (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤ ፲፮ - ፲፯) በማለት ያስረዳል።

ትምህርት አንጻራዊ የኾነ ወጥነት ያለው አወንታዊ የጠባይ ለውጥ ነው። ከስሕተት ወደ ዕውቀት፣ ካለማወቅ ወደ ማወቅ፣ ክፋውን ከደጉ፣ እሳቱን ከውኃው መለየት መቻል ነው። በዚህ መሠረት ቅዱስ ያሬድ "ከስሕተት አንተን ወደ ማወቅ መልሰኝ" ይልና ከስሕተት የተመለሱ በርከት ያሉ ሰዎችን እየጠቀሰ "እኔንም እንደ እነርሱ መልሰኝ" እያለ ይናገራል።

የተዘረዘሩት ሰዎች በቀራጭነት የነበረው በኋላ ከዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት አንዱ የኾነው ማቴዎስ[8]፣ በፊት ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረው በጥንት ስሙ ሳውል በኋላ ስሙ ደግሞ ጳውሎስ[9] የተባለው እንዲሁም ዕድሜ ልኩን ሰው ሲገድልና እየዘረፈ ሲበላ የኖረው በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰቀል በቀኙ የተሰቀለው፣ አምኖ በመመለሱም "ዛሬ ከእኔ ጋራ በገነት ትኖራለህ" የተባለው ሽፍታ[10] ናቸው።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ኹሉ የቀደመ ታሪካቸው ጥሩ ያልነበረ፣ ምንም እንኳን መደበኛ ትምህርት ቤት ገቡ ተብሎ ባይነገርላቸውም በልዩ ልዩ መልኩ ተምረው የተለወጡ ናቸው። የተለወጡት ደግሞ መደበኛም ኾነ ኢመደበኛ ትምህርት ተምረው ነው። ስለዚህ ቅዱስ ያሬድም እንደ እነርሱ ከስሕተት "አንተን ወደ ማወቅ መልሰኝ" እያለ ይናገራል። ስለዚህ ትምህርት ማለት ካለማወቅ ወደ ማወቅ፣ በጨለማ ከሚመሰለው ድንቁርና በብርሃን ወደሚመሰለው ዕውቀት መመለስ ነው።

## መደበኛ ትምህርት

ትምህርት በመደበኛም ኾነ በኢመደበኛ የሚገኝ ዕውቀት ነው ብለናል። በመደበኛ የሚገኘውን ትምህርት ቅዱስ ያሬድ በመጽሐፉ፡- "ኒቆዲሞስ ስሙ መልአኮሙ ለአይሁድ ዘሖረ ኀቤሁ ለኢየሱስ ቀዲሙ ሌሊተ ወይቤሎ ረቢ ነአምን ብከ ከመ እምኀበ አብ መጻእከ ከመ ትኩን መምህረ ወበምጽአትከ አብራህከ ለነ ወሰላመ ጸጎከነ አንሥእ ኃይለከ ወነአ አድኅነነ" ("ስሙ ኒቆዲሞስ የሚባል የአይሁድ አለቃ አስቀድሞ ሌሊት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሄዶ መምህር ሆይ መምህር ትኾን ዘንድ ከአብ ዘንድ እንደ መጣህ እናምናለን አለው፤ በመምጣትህም አበራኽልን፤ ሰላምንም ሰጠህን፤ ኃይልህን አንሣ ናና አድነንም") (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፥፻፳፭) በማለት ይገልጸዋል።

ኒቆዲሞስ ቀን፣ ቀን ከአይሁድ ጋራ እየዋለ የሚመክር፣ የአይሁድ አለቃ ኾኖ አይሁድን ያስተዳድር የነበረ ነው። ሌሊት፣ ሌሊት ደግሞ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እየሄደ ይማር የነበረ ሰው ነው። ይህ ሰው ሌሊት ሌሊት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እየሄደ ሲማር አስቀድሞ መምህርነቱን ማመኑን፣ መምህር ኾኖ ከአብ ዘንድ እንደ ተላከ የተናገረው

[8] ጌታችን ኢየሱስም ከዚያ ዐልፎ ስሙ ማቴዎስ የተባለ ሰው በቀረጥ መቀበያው ተቀምጦ አገኘና "ተከተለኝ" አለው፤ ተነሥቶም ተከተለው (ማቴ. ፱፣ ፱)።

[9] ሳውል ግን የጌታን ደቀ መዛሙርት ለመግደል ገና እየዛተ ወደሊቀ ካህናቱ ሄደ። ምን አልባት በመንገድ የሚያገኘው ሰው ቢኖር ወንዶችንም ሴቶችንም እያሰረ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸው ዘንድ በደማስቆ ላሉት ምኵራቦች የሥልጣን ደብዳቤ ከሊቀ ካህናቱ ለመነ (ሐዋ. ፱፥፩-፪)።

[10] ዐብረው ተሰቅለው ከነበሩት አንዱ ወንበዴ "አንተስ ክርስቶስ ከኾንኽ ራስኽን አድን፤ እኛንም አድነን"፤ ብሎ ተሳደበ። ኋደኛውም መልሶ ገሠጸው፤ እንዲህም አለው። "አንተ እግዚአብሔር አምላክኽን አትፈራውምን? በእኛስ በሚገባ ተፈርዶብናል፤ እንደ ሥራችንም ፍዳችንን ተቀበልን፤ ይኽ ግን ምንም የሠራው ክፉ ሥራ የለም" (ሉቃ. ፳፫፥፴፱-፵፪)።

በቅዱስ ወንጌል ተጽፏል። የቅዱስ ያሬድ በዚህ መጽሐፍ ይህን መጥቀስ መጽሐፉ ለማኅበራዊ ፋይዳ ላለው አበርክቶ አብነት ሊኾን ይችላል።

ኒቆዲሞስ ማታ ማታ እየሄደ ይማር እንደ ነበረ ዛሬም በአብነት ትምህርት ቤት ትምህርቱ የቀንና የሌሊት ተብሎ ተከፈለ። በቃል የሚያዘውን ሌሊት ሌሊት ሲማሩት በቃል መያዝ የግድ የማያስፈልገውን ደግሞ ቀን ቀን መጽሐፍ ዘርግተው ይማሩታል። እንዲሁ በዘመናዊውም ሰዎች ቀን ቀን ሌላ ሥራ እየሠሩ ማታ ማታ ይማራሉ። በመጽሐፉ ላይ ያለው ፅንሰ ሐሳብና በአብነት ትምህርት ቤትም ያለው የትምህርት ሥርዐት ለእንደዚህ ያለው ለዘመናዊው የትምህርት ሥርዐት መሠረት እንደ ኾነ ማሳያ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ጉዳይ መምህሩ አለ፤ ተማሪው አለ፤ የትምህርት ሰዓቱ ተጠቅሷል፤ ትምህርቱም እንደዚሁ። ስለዚህ ይህንም መደበኛ ትምህርት ልንለው የምንችለው ነው።

## ኢመደበኛ ትምህርት

ትምህርት በብዙ መንገድ ይገኛል፤ አስተማሪውም በብዙ መልኩ ሊያስተምር ይችላል። ተማሪውም በቀጥታ መደበኛ ትምህርት ቤት ገብቶ ከሚማረው በተጨማሪ በኢመደበኛ መልኩ የሚማረው ብዙ ነው። ሥርዐተ ትምህርት የማይቀረጽለት፣ የዕውቅና ማረጋገጫ የማይሰጥበት፣ በልዩ ልዩ መንገድ የሚገኘው ትምህርት ኢመደበኛ ትምህርት ተብሎ ይታወቃል። ቅዱስ ያሬድ ሰዎች በመደበኛም በኢመደበኛ መልኩም ለምሳሌ፡- በሥነ ፍጥረት መማር እንደሚችሉ ምሳሌ በመጥቀስ ያስረዳል። ለምሳሌ፡- "ፈያታዊ ዘየማን መኑ መሀረከ ወመኑ ነገረከ ከመ ታእምር ዘንተ? ነቢያተ ኢጠየቁ ወሐዋርያተ ኢተሎኩ፤ አላ ፀሓይ ቀጸበተኒ። ሶበ ርኢኩ አመንኩ ኃይለ መስቀሉ መድኃኒተ ኮነኒ" ("ፈያታዊ ዘየማን ይህን ታውቅ ዘንድ ማን አስተማረህ? ማንስ ነገረህ? ፀሐይ ጠቀሰችኝ እንጂ ነቢያትን አልመረመርኩም፣ ሐዋርያትንም አልተከተልኩም፤ የመስቀሉ ኀይል መድኃኒት ኾነኝ") ማለቱን ይነግረናል (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤፳፫)።

በዚህ ጥቅስ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀኝ በኩል ተሰቅሎ የነበረውን ወንበዴ ያገኘው ትምህርት ከምን እንደ ኾነ ሲጠይቀውና ወንበዴውም ይኽን የተማረው ነቢያትን መርምሮ ሐዋርያትንም ተከትሎ እንዳልኾነ ነገር ግን ከፀሓይ እንደ ተማረ መመለሱን ይገልጻል። ፀሐይ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰቀል ጨልማ ስለ ነበረ ርሷ የጨለመችው አምላክነቱን ብትረዳ ነው እንጂ በማለት ርሱም ሊያምን ችሏልና ትምህርት በሥነ ፍጥረትም እንደሚገኝ ይህ ድጓ ያስረዳናል።

## ሐሰተኛ ትምህርት

እውነተኛው ትምህርት በብዙ መንገድ እንደሚገኝ ኹሉ ሐሰተኛ ትምህርትም በብዙ መልኩ ይገኛል። በመደበኛውም፣ በኢመደበኛውም ሐሰተኛ ትምህርት ሊሰጥ ይችላል። በዚህ መጽሐፍም እውነተኛው ትምህርት እንዳለ ኹሉ ሐሰተኛ ትምህርትም ሊኖር እንደሚችልና ከዚያ ሐሰተኛ ትምህርት መጠንቀቅ እንደሚገባ የሚያስረዳ ክፍልም እናገኛለን። ይህንም በተመለከተ "እንዘ ይነብር እግዚእነ ውስተ ደብረ ዘይት ወይቤሎሙ ለሐዋርያት እምከመ ለምለመ አዕጹቂሁ ወበጽሐ ጊዜሁ ለማእረር ዑቁኬ ኢያስሕቱክሙ፤ አንትሙኒ ሰንበታትየ ዕቀቡ" ("ጌታችን በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ሐዋርያትን እንዲህ አላቸው፤ በለስ የለመለመ እንደ ኾነ ጊዜው እንደ ደረሰ በዚያ ታውቃላችሁ። እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ፤ እናንተም ሰንበቶቼን አክብሩ" በማለት አስረድቷል (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤፻፩)። ይህም "እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ" ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን እንዳስተማራቸው፣ ርሱ ካስተማራቸው ሌላም ሐሰተኛ ትምህርት የሚያስተምሩ ሐሰተኛ መምህራን እንዳሉ ይህንም ሐሰተኛ ትምህርት ተምረው እንዳይሰናከሉ መጠንቀቅ እንዳለባቸው የገለጸበት ነው።

## ፖለቲካ

ፖለቲካ የሚለው ቃል በ"ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት" (፲፱፻፸፰፤ ፷፻፰) እንዲህ ተገልጾ እናገኘዋለን። ፖለቲካ "ፖሊቲ" ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲኾን ይህም የጥንታዊት ግሪክ ትናንሽ መንግሥታት መጠሪያ ነበር። ፖለቲካ የኅብረተሰብን አደረጃጀት፣ የመንግሥትን ይዘት፣ ዓይነት፣ ቅርጽና ተግባር፣ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች መሠረታዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የሚያደርጉትን ትግል፣ በመንግሥታት መካከል የሚፈጠሩትን ግንኙነቶች ማለትም የውጭ ግንኙነቶች ፖሊሲንም በሚመለከት የተወሰነ መደብ የሚኖረውን ንድፈ ሐሳባዊ ግንዛቤና ከዚሁ የሚመነጨውን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያጠቃልላል።

ከላይ በተጠቀሰው ሐሳብ በርከት ያሉ ነጥቦችን የምናገኝ ቢኾንም በዋናነት ፖለቲካ ማለት ማኅበራዊ መዋቅርን፣ መንግሥታዊ አደረጃጀትን፣ በመንግሥታዊ አደረጃጀትና በማኅበራዊ መዋቅር መካከል የሚኖረውን ግንኙነት፣ ማኅበራዊ መዋቅሩ ጥቅሙን ለማስከበር ሲል የሚያደርገውን ትግል ወዘተ. የሚያካትት እንደ ኾነ መረዳት ይቻላል። ፖለቲካ ሲነሣ ልብ ሊደረጉ የሚገቡ ነገሮች አሉ። መሪው ለሕዝቡ ሊያደርገው የሚገባ ነገር እንዳለ ኹሉ ሕዝቡም ለመሪው ሊያደርገው የሚገባ ነገር አለ። በተመሪው ወይም በሕዝቡ በኩል ያለውን ለመመልከት በሮሜ (፲፫፣፭-፯) እንዲህ ተብሎ የተጻፈውን ትእዛዝ መነሻ እናድርግ፣ "ስለዚህ ቍጣን ስለመፍራት ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን

ስለ ኀሊና ደግሞ መገዛት ግድ ነው። ስለዚህም ግብር ታገቡላቸዋላችሁ፤ ለዚህ ሥራ የተሾሙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና፤ ለኹሉም እንደሚገባው አድርጉ፤ግብር ለሚገባው ግብርን ስጡ፤ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን ስጡ፤ ዐሥራት ለሚገባው ዐሥራትን ስጡ፤ ሊፈሩት የሚገባውን ፍሩ፤ ክብር የሚገባውንም አክብሩ" እንዲል። በዚህ መሠረት ለመሪዎች መገዛት፣ መሪዎችንም ከሚገባው በላይ ሳይኾን በሚገባ ማመስገን እንደሚያስፈልግ በዚህ መጽሐፍ ተገልጿል።

በማርክሲዝም ሌኒንዝም መዝገበ ቃላትና በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሰው ፅንሰ ሐሳብ በመነሣት ፖለቲካ በሕዝብና በመንግሥት መካከል የሚኖር ግንኙነት፣ ማኅበራዊና መንግሥታዊ መዋቅር የሚመሠረትበት፣ መሪዎቹ ለሕዝቡ ሕዝቡ ለመሪዎቹ የሚያከናውኑትን ተግባር ኹሉ አጠቃልሎ የያዘን ሰፊ ፅንሰ ሐሳብ ያካተተ ንድፈ ሐሳብ ነው።

### ለንጉሥ የሚገባ ምስጋና

ከላይ እንደ ተገለጸው ለንጉሡ ክብር ይገበዋል። ይህንም በተመለከተ ያሬድ፡- "ፀሓይ ዘኢየዐርብ፤ ማኅቶት ዘኢይጠፍእ፤ ባዕል ውእቱ ዘኢይሌቅሕዎ፤ ሠርጎሙ ለሐዋርያት፤ ንዋየ ነዳያን ወምስካየ ግፉዓን። ሠርከ ነአኵተከ። መሓሪ ንጉሥ ዘኢይትኄየይ ተግባሮ"፤ ("የማይጠፋ ፀሐይ ነው፤ የማይጠልቅ መብራት ነው፤ የማያበድሩት ባለጸጋ ነው፤ የሐዋርያት ሽልማታቸው ነው፤ የችግረኞች ገንዘብ ነው፤ ለተገፉት መጠጊያ ነኽ፤ ሥራህ የማይቋረጥ አንተ ይቅር ባይ ነኽ፤ ንጉሥ ኹል ጊዜ አንተን እናመሰግናለን" በማለት በጾመ ድጓ የተናገረውን እናገኛለን (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤፳፩)።

ይህ ቃል በርግጥ በቀጥታ የተነገረው ለኢየሱስ ክርስቶስ ነው። "ንጉሠ ሰማያት ወምድር" ይባላልና ለርሱ የተናገረው ነው። ይኹን እንጂ በንግሥናው ለርሱ የተነገረው ምስጋና እና አክብሮት በዚህ ዓለም ላሉ ነገሥታት ኹሉ የሚነገር ነው፤ ስለዚህ ከላይ የተጠቀሰውን የቅዱስ ያሬድን ቃል ስንመለከት እጅግ በሚገርም ኹኔታ ለነገሥታትና ለመሪዎች የሚደረገውን ምስጋና እንመለከታለን።

### የአቀባበል ሥርዓት

በዚህ መጽሐፍ ለገዢዎች የሚደረገውን ክብርና ምስጋና በተመለከተ እንመለከታለን። ገዢዎች የኹሉንም ሕዝብ ፍላጎት ማሟላት አይችሉም፤ ኹሉንምም አያስቀይሙም። ይኹን እንጂ ከፊሉን ሊያስደስቱ ከፊሉን ደግሞ ሊያስቀይሙ ይችላሉ። ሕዝቦች ለሚያስደስቷቸው መሪዎች መልካም አቀባበል ሲያደርጉላቸው፤ የሚያስቀይሟቸውን ደግሞ ተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ያደርጉባቸዋል። በአንድ ወቅት ተደስቶ መልካም

አቀባበል ያደረገውም በሌላ ጊዜ ተቀይሞ ተቃውሞውን ሲያሰማ ይስተዋላል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ኹለቱንም ድርጊት፡- "ወእንዘ ስሙን በዓለ ፋሲካ … ወተቀበልዎ ሕዝብ ብዙኃን አእሩግ ወሕፃናት ነሚኦሙ አዕጹቀ በቀልት፣ እንዘ ይብሉ ሆሳዕና በአርያም ተጽዒኖ ዲበ ዕዋል ቦአ ሀገረ ኢየሩሳሌም በትፍሥሕት ወበሐሤት ይሁቦሙ ኃይለ ወሥልጣነ" ("በፋሲካ በዓል ሳምንት… ሕፃናት፣ አረጋውያንና ብዙ ሕዝብ የዘንባባ ቅጠል ይዘው ሆሳዕና በአርያም እያሉ ተቀበሉት፡፡ በአህያ ውርንጭላም ተጭኖ ኢየሩሳሌም ገባ፤ በደስታና በሐሤት ኀይልንና ሥልጣንን ይሰጣቸዋል") ተብሎ በጾመ ድጓ ተጽፎ እናገኛለን (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤፻፺)፡፡

ይህ ዛሬ በዘመናችን መሪዎችን ለመቀበል ሕፃናቱ አበባ ይዘው፣ የአበባ ምንጣፍ ተጎዝጉዞለት፣ መሪውን የሚመጥኑ ታላላቅ ባለሥልጣናትም በተገኙበት ሕዝቡ ኹሉ በሚችሉት ነገር እያመሰገኑ የሚያደርጉትን የክብር አቀባበል ያጠይቃል፡፡

## መንግሥትን መቃወም

ፖለቲካ በመንግሥታዊ መዋቅርና በማኅበራዊ መዋቅር መካከል ያለውን አወንታዊም ኾነ አሉታዊ ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ መንግሥት ደጋፊ እንዳለው ኹሉ ተቃዋሚም አለው፡፡ ከላይ ድጋፎቹን፣ ለርሱ የሚደረጉ ምስጋናዎችን ተመልክተናል፡፡ በሌላ መልኩ ሕዝብ መሪው አልመችህ ሲለው ራሱ የሰጠውን ሥልጣን ይነጥቃል፡፡ ራሱ ካልሾመውና ሥልጣኑን ካልሰጠው ደግሞ "በምን ሥልጣንህ እኛን ትመራለህ?" "በእኛ ላይ ማን ሾመህ?" እያለ የተቃውሞ ጥያቄ ማንሣቱ አይቀርም፡፡ መጽሐፉ በዚህ መንገድም ተቃውሞን በሚመለከት የሚያነሣው ጉዳይ አለው፡፡ "አምላኩሰ ለአዳም ለዕረፍት ሰንበተ ሠርዐ ወይቤልዎ አይሁድ በአይ ሥልጣን ትገብር ዘንተ ወይቤሎሙ ኢየሱስ አነኒ እገብር አንትሙኒ እመኑ ለግብርየ…" ("የአዳም አምላክ ለዕረፍት ሰንበትን ሠራ፤ አይሁድም በምን ሥልጣንህ ይህን ትሠራለህ? አሉት፤ ኢየሱስም እኔ እሠራለሁ እናንተም ሥራዬን ዐይታችሁ እመኑ") አላቸው (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤፹)፡፡

## ሰላምን ማስከበር

"ንጉሥ ጸግወነ ሰላመ ኑፈር ወንእቱ በሰላም፣ አኑመነ በሰላም ኑፈር ወንእቱ በሰላም" ("ንጉሥ ሆይ ሰላምን ስጠን፤ በሰላም እንሠማራ፤ በሰላምም ወደ ቤታችን እንግባ፤ በሰላም እንተኛ በሰላምም ወጥተን እንገባ ዘንድ") (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤፱)፡፡ አንድ ሀገር በትክክልም "ጠንካራ መሪ አላት"፤ "ልማቱ እያደገላት ነው"፤ "በሥልጣኔ እያደገች ነው" የሚባለው በመጀመሪያ ሕዝቡ በሰላም ወጥቶ መግባት ሲችል ብቻ ነው፡፡ መሪውም ሕዝቡ በሰላም ወጥቶ እንዲገባ፣ ሠርቶ እንዲያደግ፣ ሕይወቱን በሰላም እንዲመራ

ይችል ዘንድ ሰላምን ማስከበር የመጀመሪያና ተቀዳሚ ተግባሩ ነው። ከላይ የተጠቀሰው የቅዱስ ያሬድ አገላለጽም የሚያስረዳን ይህን ነው።

**ዲሞክራሲን ማስፈን**

በዲሞክራሲ ፅንሰ ሐሳብ አንድ መንግሥት የሚመራውን ሕዝብ መብትና ግዴታ በማሳወቅ ሕዝቡ መብቱን በሚገባ እንዲጠቀም ግዴታውንም በአግባቡ እንዲጠብቅ ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህ የሚኾነው ደግሞ የፍትሕ ሥርዐቱን በአግባቡ ማሰተናገድ ሲችል ነው። ፍትሕን በተመለከተ ቅዱስ ያሬድ በጾመ ድጓ መጽሐፉ ምን መኾን እንደሚገባው "መኰንን ዘበርቱዕ ይኴንን ወኢያደሉ ለገጽ ንጉሥ ንሕነ ኀቤከ ተማሕፀነ"፤ ("በርትዕ በአግባቡ የሚገዛ ገዢ፤ ፊት ዐይቶ የማያዳላ ንጉሥ እኛ ወዳንተ ተማፀንን" በማለት ያስረዳል (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፥፶፫)። ይህ አንዱ የእውነተኛ መሪ መለኪያ ነው።

በሌላ በኩል ቅዱስ ያሬድ በመጽሐፉ ላይ ፍትሕ የተጓደለባቸው አካላት እንደ ነበሩም ያስረዳል። "ከልሐ ዕውር በውስተ ፍኖት ወገሠጽዎ እለ ይመርሕዎ ከመ ያርምም ወአዕበየ ከሊሐ እንዘ ይብል ተሣሀለኒ እግዚእየ ወልደ ዳዊት ርድአኒ" ("ዕውሩ በመንገድ ላይ ሳለ ጮኸ፤ የሚመሩት ዝም ይል ዘንድ ከለከሉት። ርሱ ግን የዳዊት ልጅ ማረኝ እያለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጮኸ") (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፥፹) እንዲል። ይህን ጥቅስ በጥልቀት ብንመለከተው ምን አልባትም የአሁኑን ወቅት የሚያስታውሰን ይመስለኛል፤ ምክንያቱም የተበደለው "ተበድያለኹ" ብሎ እንዳይጮኽ የበደሉት ቀድመው ይጮኻሉ። ያም ባይኾን የተበደሉት እንዳይጮኹ የሚከለክላቸው ኃይል ይወጣና "በደላችኹን አትናገሩም"፤ "ዝም በሉ" እያለ ሲከልክል ይስተዋላል። ስለዚህ ይህ በወቅቱ የነበረውን የፍርድ መጓደል የሚያመለክት ነው። ፍትሕ ሲጓደል በደለኛ በደሉን ተናግሮ እውነተኛ ፍርድ አለማግኘት ብቻ ሳይኾን መጮኽ አለመቻልም፣ እንዳይጮኹ መከልከልም ይስተዋላል።

**እንስሳትን ስለ ማክበር**

የሠለጠኑት ሀገራት ከሚመሰገኑባቸውና "ሠልጥነዋል" ከሚባሉባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የሰውን መብት ብቻ ሳይኾን የእንስሳትንም መብት ማስከበር መቻላቸው ነው። ቅዱስ ያሬድ በዚህ መጽሐፍ የእንስሳት መብት ሳይቀር መከበር እንዳለበት ያስረዳል። "አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ወይቤሎ ሰብእከ ወላሕምከ ወኵሉ ቤትከ ያዕርፉ በሰንበት"፤ ("እግዚአብሔር ሙሴን አዘዘው፤ ቤተ ሰብኽም እንስሳኽም በቤትኽ ያለ ኹሉ በሰንበት ይረፉ") እንዲል (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፥፩)። የሰው ልጅ እንስሳትን እንዲገለገልባቸው ተፈቅዶለታል። ይኹን እንጂ በአግባቡ እንዲገለገልባቸው እንጂ

ከሕግ በላይ እንዲገለገልባቸው አይፈቀድለትም። እርሱ ዕረፍት እንደሚያስፈልገው ኹሉ ለእንስሳትም የዕረፍት ጊዜ እየሰጠ፣ እርሱ ምግብ እንደሚያስፈልገው ኹሉ ለእንስሳትም ምግብ እየሰጠ እንዲገለገልባቸው እንደ ተፈቀደለት ቅዱስ ያሬድ በዚህ መልኩ ያስረዳል።

## ሀገርን ስለ መጠበቅ

የማንኛውም ሀገር ገዢ የሀገሩን ሉዓላዊነት አስጠብቆ መኖር የግድ ነው። የሀገሩ ሉዓላዊነት እየተደፈረ እያየ ዝም የሚል መሪ መሪ ሊባል አይችልም። በቅዱስ ያሬድ መጽሐፍ የአንድ ሀገር ገዢ የሀገሩን ሉዓላዊነት ሲያስከብር ምን ሊባል እንደሚችል ያስረዳል። "ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር በካህናት ሕጽርት ወበመንፈስ ቅዱስ ክልልት፤ ንጉሥኪ ጽዮን ኢይትመዋእ ለፀር ወኢየኀድጋ ለሀገር" ("የእግዚአብሔር የሕጉ ታቦት በካህናት የታጠረች፣ በመንፈስ ቅዱስ የተከበበች ናት፤ ጽዮን ሆይ ንጉሥሽ ለጠላት አይሸነፍም፤ ሀገርንም አይተዋትም") እንዲል (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፥፻፹፬)። ይኽ መልእክት የመሪውን ጥንካሬ፣ ቆራጥነት፣ ደፋርነት፣ አይበገሬነት ወዘተ. የሚያስረዳ ነው። በሀገራችን የውጭ ጠላት እየመጣ ወረራ ለማድረግ በሞከረ ጊዜና ነገሥታቱ ሠራዊታቸውን አሰልፈው በመዋጋት ድል ባደረጉ ጊዜ የጀግንነት መዝሙር ተዘምሮላቸዋል፤ የጀግንነት ሙዚቃ ወጥቶላቸዋል።

## ስለ ሃይማኖት

ሃይማኖት "ሀይመነ አሳመነ" ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲኾን ማመን መቀበል፣ በዐይን የማይታየውን፣ በእጅ የማይዳሠሠውን ይኾናል ብሎ መቀበል፣ ተስፋ ማድረግ ማለት ነው። ከላይ በተጠቀሰው የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ደግሞ የሚታመነው ማን እንደ ኾነ ሲያስረዳ ኹሉን በፈጠረ፣ ኹሉን በሚገዛ፣ በእግዚአብሔር አብ ማመን፣ ከእግዚአብሔር አብ በተወለደው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ሃይማኖት እንደሚባል ይነግረናል። ኪዳነ ወልድ (፲፱፻፵፰፥ ፫፻፰፱) በበኩላቸው ሃይማኖት፡- "በቁሙ ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ ጽኑ ተስፋ፣ የአምልኮት ባህል፣ በልብ በረቂቅ ሐሳብ የሚሣል፤ ሃይማኖት ቅድስት ምስጢረ ሥላሴ፣ ምስጢረ ሥጋዌ፤ ሃይማኖት ርትዕት ኦርቶዲክሳዊት፣ የኦርቶዶክስ ባህል") በማለት ይፈቱታል። በዚህ ጥናት ቅዱስ ያሬድ በመጽሐፈ ጾመ ድጓ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ምን ያህል አጽንዖት ሰጥቶ አንሥቷቸዋል? የሚለውን እንመለከታለን።

መጽሐፉ ገና ሲጀምር "ሃሌ ሃሌ ሉያ ዘወረደ እምላዕሉ አይሁድ ሰቀሉ ወሚመ ኢያእመሩ እግዚአ ኵሉ ዘያሐዩ በቃሉ"፤ ("ቅድመ ዓለም የነበረው ዛሬም ያለው ዓለምን

አሳልፎ የሚኖረው ከላይ የወረደው ነው። አይሁድ ሰቀሉት፣ የኹሉ ጌታ በቃሉ የሚያድን እንደ ኾነ ግን ምንም አላወቁም”) በማለት ነው (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤፩)። ከላይ እንደ ተገለጸው ሃይማኖት በሥላሴ አንድነት ሦስትነት ማመን ከሦስቱ አካል አንዱ ወልድ ከሰማየ ሰማያት መውረዱን ከድንግል ማርያም በሥጋ መወለዱን፣ ሰው ኾኖ በሞቱ ዓለምን ማዳኑን ወዘተ. አምኖ መቀበል ነው። ቅዱስ ያሬድም የገለጸው ይኽንን ነው።

በትምህርተ ሃይማኖት ዋናው ጉዳይ “ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የለም” ብሎ ማመን ነው። እንዲያውም ከዚህ ጋራ ተያይዞ በትውፊት “ኀልማሳ በሚስቱ፣ ንጉሥ በመንግሥቱ አምላክ በአምላክነቱ ቢገቡበት አይወድም” እየተባለ ይነገራል። ከዚህ ጋራ በተያያዘ ጾመ ድጓ ፡- “እግዚአብሔር አምላክ ቀናኢ ውእቱ፤ ኪያሁ አምልኩ፤ ለባሕቲቱ ተቀነዩ ወሎቱ ሡዑ ወአክብሩ ሰንበተ በጽድቅ፤ እስመ አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌሁ ዘየዐቅብ ኪዳኖ በጽድቅ ዘለዓለም፤ ይከድነከ በየማኑ” (“እግዚአብሔር አምላክ ቀናተኛ አምላክ ነው፤ ርሱን ብቻ አምልኩ ለርሱም ሰዉ፤ ሰንበትንም በእውነት አክብሩ፤ ከርሱ በቀር ኪዳኑን ለዘለዓለም የሚጠብቅ ሌላ አምላክ የለምና፤ በቀኙም ይጋርድሃልና”) እንዲል (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤፯)።

## ስለ ምጣኔ ሀብት

ምጣኔ ሀብት ኢኮኖሚ ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በአቻነት የወሰድኩት ነው። ምጣኔ ሀብት ማኅበራዊ ሳይንስ ነው። በሌላ አነጋገር በሳይንሳዊ ዘዴ ላይ የተመሠረተ፣ በጠንካራ ትንተና ላይ በመመርኮዝ የሰውን ባሕርይ የሚያጠና ስልታዊ ምርመራ ነው። ምጣኔ ሀብት አብዛኛው የንግድ ዘርፎች የተነሡበት ወይም የብዙ የንግድ ዘርፎች አስገኚ ወላጅነው። ብዙ ሰዎች ምጣኔ ሀብት የሚለው ቃል ምን ማለት እንደ ኾነ አንድ ወጥ ሐሳብ የላቸውም።

ምጣኔ ሀብት ያልተገደቡ የሰው ልጆች ፍላጎቶችን ለማሟላት ያሉ ሀብቶችን በተገቢ ኹኔታ ለማደላደል የሚረዳ የጥናት መስክ ነው። በሌላ አነጋገር ምጣኔ ሀብት የሰው ልጅ ለመኖር የሚፈልጋቸውን ነገሮችን ኹሉ የሚመለከት በመኾኑ የሰውን ባሕርይ ማጥናት ነው ማለት ይቻላል። ለሰው ልጅ የሚያስፈልገው የሀብት አቅርቦት እንደ ልብ ሊገኝ የማይችል ውስን ነው፤የሰው ፍላጎት ደግሞ ከዚያ በላይ ያልተገደበ ነው። ከሰው ልጅ ፍላጎት አንጻር ሲጠና ያለው ውስን ሀብት ስለ ኾነ በምጣኔ ሀብት ጥናት የሰው ልጅ ፍላጎትና ያለው የሀብት መጠን እንዲጣጣም ማድረግ ነው (ዲልትስ፣ ፳፻፩፣ ፩፪)። በምጣኔ ሀብት ፅንሰ ሐሳብ ሀብት ከሚሰበሰብባቸው መንገዶች መካከል አንዱ ንግድ ነው። ንግድ ደግሞ በሕጋዊ መልኩ ሊከናወን የሚገባው ሙያ ቢኾንም በሕገ ወጥ

መልኩም ሊከናወን ይችላል። በቅዱስ ያሬድ የጾመ ድጓ መጽሐፍ ሕጋዊ የኾነው ንግድ የተበረታታበትን፣ ሕገ ወጥ የኾነው ደግሞ የተነቀፈበትን ሐሳብ እናገኛለን።

### የንግድ ሥርዓቱን መከታተል

መንግሥት በፈቀደው ቦታ፣ ጊዜና ኹኔታ ላይ የተመሠረተ፣ በማኅበረሰቡ ዘንድም ተቀባይ የኾነ ሲኾን ሕጋዊ ነውና ማበረታታት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ባልተፈቀደ ቦታ፣ ጊዜና ሕጋዊ የኾነ የሕግ ፈቃድ ሳይኖረው የሚነግድ ከኾነ ደግሞ ሕገ ወጥ ንግድ ነውና መቈጣጠር ያስፈልጋል። ቅዱስ ያሬድ በጾም ድጓው ኹለቱንም በተመለከተ፡- "መኑ ውእቱ ገብር ኄር ወምእመን ዘይረክቦ እግዚኡ በምግባረ ሠናይ ወይሠይሞ ዲበ ኵሉ ንዋዩ ካዕበ ይቤሎ እግዚአብሔር ገብር ኄር ወምእመን ዘበውኁድ ምእመነ ኮንከ ዲበ ብዙኅ እሠይመከ ባእ ውስተ ፍሥሓሁ ለእግዚእከ" ("ጌታው በበጎ ምግባር የሚያገኘው ቸርና ታማኝ አገልጋይ ማን ነው? እርሱን በገንዘቡ ኹሉ ላይ ይሾመዋል። ዳግመኛም እግዚአብሔር ቸርና ታማኝ አገልጋይ ሆይ በጥቂቱ ታምነኻልና በብዙ እሾምሃለኹ። ወደ ጌታኽ ደስታ ግባ") ብሏል (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤፻፵፫) ።

በዚህ ምንባብ መልካም አገልጋይ ወይም ሕጋዊ ነጋዴ የተበረታታበት፣ በታማኝነቱና በቸርነቱ የማበረታቻ ሽልማት ያገኘበት ኹኔታ መኖሩን እንረዳለን። በሌላ በኩል ደግሞ ሕጋዊ ባልኾነ መልኩ ይነግዱ የነበሩትን በሚከተለው መልኩ ወቅሷቸዋል። "ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአይሁድ አነ ውእቱ እግዚኣ ለሰንበት፤ ኢትግበሩ ቤተ አቡየ ቤተ ምሥያጥ ቤትየሰ ቤተ ጸሎት ይሰመይ" ("ኢየሱስ አይሁድን አላቸው፤ የሰንበት ጌታ እኔ ነኝ፤ የአባቴን ቤት የገበያ ቦታ አታድርጉ፤ ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላልና") (መንግሥቱ፣ ፳፻፱፤፶፰)።

## 4. ማጠቃለያ

ጥናቱ መጽሐፈ ጾመ ድጓ ከማኅበራዊ ፋይዳ አንጻር ስላለው ይዘት በርካታ ጉዳዮችን ተመልክቷል። ቅዱስ ያሬድ በመጽሐፈ ጾመ ድጓው ማኅበራዊ ትስስርን፣ ትምህርትንና ትምህርት ነክ ጉዳዮችን፣ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን፣ ምጣኔ ሀብታዊ ጉዳዮችን፣ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ወዘተ. በሰፊው እንደ ተመለከተ የጥናቱ ግኝት ያስረዳል። ጥናቱ ካመለከታቸው ጉዳዮች በመነሣት ቅዱስ ያሬድን ለመረመረው ሰው በአንድ በድጓ ብቻ የሥነ ማኅበረሰብ፣ የሥነ ትምህርት፣ የሃይማኖት፣ የምጣኔ ሀብት፣ የፖለቲካል ሳይንስ ወዘተ. ኹሉ ባለሙያ ኾኖ ያገኘዋል። የቅዱስ ያሬድ መጽሐፈ ጾመ ድጓ ማኅበራዊ ፋይዳው እጅግ የላቀ እንደ ኾነ ከጥናቱ ለመረዳት ተችሏል። የሰው ልጅ በማኅበር ሲኖር ከሚያስፈልጉት ጉዳዮች መካከል በርካታዎቹ የተካተቱበት መጽሐፍ መኾኑን ጥናቱ

አሳይቷል። ከላይም እንደ ተገለጸው የማኅበራዊ ትስስር ጉዳይ፣ የትምህርት ጉዳይ፣ የሃይማኖት ጉዳይ፣ የምጣኔ ሀብት ጉዳይ፣ የፖለቲካ ጉዳይ፣ የመጠለያ ጉዳይ ወዘተ. ኹሉ በስፋትና በጥልቀት የተካተቱበት መጽሐፍ ነው። ይህም ከላይም በአቶ ቴዎድሮስ ገብሬ እንደ ተገለጸው ሥነ ጽሑፍ ከሌሎች ሙያዎች በላቀ ከሰው ልጅ ህልውና ጋራ ፍጹም የተቆራኘ መኾኑን፣ የሰውን ልጅ ሕይወት ከልደት እስከ ሞት ባለው ብቻ ሳይወሰን ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ዘለዓለማዊ ሕይወትም የሚቃኝ አይመለከተኝም የሚለው አንድም የኑሮ ፈር፣ አንድም የሕይወት ፈርጅ እንደሌለው የሚያጠይቅ ግሩም መጽሐፍ ነው።

በዚህ ጥናት ቅዱስ ያሬድ በሥነ ጽሑፉ ያለውን ማኅበራዊ አተያይ እጅግ የመጠቀና የጠለቀ እንደ ኾነ በትንታኔው ላይ በተነሡት ማሳያዎች ማለትም አንድ ማኅበረሰብ ትስስር ከሚፈጥርባቸው ከትምህርት፣ ከማኅበራዊ ዝምድና፣ ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ፣ ከምጣኔ ሀብት ወዘተ. አንጻር እጅግ የጠለቀና የመጠቀ እንደኾነ ማመላከት ተችሏል፤ በመኾኑም መጽሐፉ ዘመናዊው ሥነ ጽሑፍ ተጀመረ ባልተባለበት ዘመን የነበረ፣ ነገር ግን ዘመናዊ ሥነ ጽሑፍ ተጀመረ ከተባለበት ዘመን ጀምሮ የተጻፉት የሥነ ጽሑፍ መጻሕፍት ሊዳሥሡት የሚገባውን ጉዳይ በመዳሠሥ ፈር ቀዳጅ የኾነ፣ በሥነ ጽሑፍ ማኅበራዊ፣ መንፈሳዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖለቲካዊ ወዘተ. ጉዳዮችን ኹሉ መዳሠሥና መተቸት እንደሚቻል መንገድ ጠራጊ በመኾን ዓላማዪ ተብሎ ከተጻፈለት ሃይማኖታዊ ዐውድ በተጨማሪ በርካታ ማኅበራዊ ጉዳዮችን የሚዳሥሥ መጽሐፍ እንደ ኾነ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል።

## ዋቢ ጽሑፎች

ልሳነ ወርቅ ገብረ ዮሐንስ (መሪጌታ)፡፡ (፲፱፻፺፯)፡፡ ጥንታዊ ሥርዓተ ማኅሌት ዘአቡነ ያሬድ ሊቅ፡፡

መንግሥቱ ገብረ አብ (መምህር)፡፡ (፳፻፱)፡፡ ጾመ ድጓ ዘቅዱስ ያሬድ (ኹለተኛ ዕትም)፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ደርጅት፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ (፳፻፰)፡፡ በይነ ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ፡፡ ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡ (፲፱፻፹፰)፡፡ *ወንጌል ቅዱስ፤ ንባብና ትርጓሜው፡፡* ብርሃንንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)፡፡ *(፳፻፲፫)፡፡ መጽሐፈ ቅኔ (ዝክረ ሊቃውንት) (ክፍል ኹለት)፡*፡ዝኅራ የመጻሕፍት መደብር፡፡

*መጽሐፍ ቅዱስ ሰማንያ አሐዱ፡፡* (፳፻)፡፡ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡

እጓለ ገብረ ዮሐንስ፡፡ (፳፻፫)፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፡፡ (፲፱፻፵፰)፡፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት* ሐዲስ፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ዕዝራ ሐዲስ (ሊቀ ሊቃውንት)፡፡ (፳፻፰)፡፡ ድርሳነ ቄርሎስ ወጸላድዮስ ምስለ ተረፈ ቄርሎስ፤ ንባቡና ትርጓሜው፡፡ጎንደር ማተሚያ ቤት ፡፡

ጌታኹን ደምፀ (ሊቀ ጉባኤ)፡፡ (፳፻፲)፡፡ *ኆኅተ ስብከት ዘቅዱስ ያሬድ፡፡* ፋር ኢስት ትሬዲንግ፡፡

ጥዑመ ልሳን ካሳ (ርእሰ ደብር)፡፡ (፲፱፻፹፩)፡፡ *ያሬድና ዜማው፡፡* ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

መጻሕፍተ ብሉያት ፪ቱ እሉ እሙንቱ ኦሪት ዘፍጥረት *(ዘልደት)* ኦሪት ዘፀአት፤ (*አንድምታ ትርጓሜ)፡፡* (፲፱፻፺፱)፡፡ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፡፡

*መጽሐፈ ስንክሳር በግእዝና በዐማርኛ ከመጋቢት እስከ ጳጕሜን፡፡* (፲፱፻፺፫)፡፡ትንሣኤ ማሳተሚያድርጅት፡፡

የማርክሲዝም ሌኒኒዝም *መዝገበ ቃላት፡፡* (፲፱፻፸፰)፡፡ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

NCERT (National Council of Educational Research and Training). (2014). Basics in Education Textbook for B. Ed. Course. NCERT.

Dilts, David A. (2004). Introduction to Microeconomics (7th edition).Indiana-Purdue University- Fort Wayne.

Lee, Ralph. (2011). Symbolic Interpretations in Ethiopic and Ephremic Literature [Unpublished doctoral dissertation].University of London, School of Oriental and African Studies.

Senkoris Ayalew Kassa. (2018). The Ethiopic Semiosis: Historical Application and Interpretation with Reference to the Hymnal Books of St. Yared [Unpublished Masters thesis].Addis Ababa University.

Sirgiw Gelaw. (2009).Historical Development of Geez Qene in Different Periods [Unpublished doctoral dissertation]. Addis Ababa University.